አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 034 ጥቅምት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ፡- ሳሙኤል ተስፋዬ

# አዲስ የሥራ ባህል የፈጠረው

## የሱማሌ የስንዴ ልማት

ጌትነት ምህረቴ

አረንጓዴ መጋረጃ የሚመስለው የስንዴ ሰብል ለጥ ባለው መሬት ላይ ተንጣሏል:: የሰብሉ ቁመና የስንዴ ማሳውን ፍሬያማነት በአደባባይ ይመሰክራል:: በሱማሌ ክልል ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቀው የስንዴ ልማት በዚህ መልኩ መልማቱ በአካባቢው ነዋሪዎችም ዘንድ አግራሞትን ፈጥሯል፤ መነሳሳትንም አጭሯል፤ ተስፋንም ሰንቋል::

«በሶማሌ ክልል የእርሻ ሥራ አልተለመደም:: አብዛኛው ሕዝብ አርብቶ አደር ነው:: ከብት፣ ፍየልና ግመል እያረባ ነው የሚተዳደረው:: በዚህ አካባቢ ያማረ የስንዴ ልማት ማየታችን እያስገረመን ነው» የሚሉት በሱማሌ ክልል ፋፈን ዞን ቱሉ ጉሌት ወረዳ ኩሉሌ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሱልጣን አብዲ ናቸው::

«በቀበሌያችን የክልሉ መንግሥት ያካሄደው የስንዴ ልማት የሚያስደስትና እንድንማርበት የሚያደርግ ውጤታማ ሥራ ነው:: እኛም ከአሁን በኋላ ምርት በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል በተግባር አይተናል» ያሉት አቶ ሱልጣን፤ «በተግባር ያየነው የስንዴ ልማት እኛም እንድናለማ መነሳሳትን ፈጥሮብናል:: ከአሁን በኋላ በእንስሳት እርባታ በመተማመን ብቻ አንተኛም፤ በዘንድሮ ዓመት ስንዴ፣ በቆሎና ማሽላ ለማምረት ተዘጋጅተናል» ሲሉ ገልጸውልናል::

ከመንግሥት ድጋፍ የምንፈልገው በብድር ትራክተር እንዲሰጠንና የመስኖ ውሃ እንዲያሟላልን ብቻ ነው የሚሉት አቶ ሱልጣን አብዲ፤ እራሳችንን ለመለወጥና ከድርቅ አደጋ ስጋት ለመላቀቅ ሌት ተቀን ጥረንና ሠርተን እንለወጣለን ሲሉ ቃል ገብተዋል::

ቀደም ሲል የሱማሌ ክልል ሲነሣ ከግጭትና ከድርቅ ጋር ተቆራኝቶ ነበር የሚሉት የሱማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሐመድ በበኩላቸው፤ ባለፈው ዓመት በተከሰተው አስከፊ ድርቅ ከሕዝባችን ብዙ ጊዜ ድርቅን ሁልጊዜ ዕርዳታ እየጠበቅን መከላከል እስከመቼ ይቀጥላል? በክልሉ ወቅት እየጠበቀ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለመከላከል ምን


አዲስ የሥራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## 10ኛው የጣና ፎረም ዜጎች በሰላምና ደህንነት ዙሪያ ሊኖራቸው በሚገባቸው ሚና ላይ ያተኩራል

-ፎረሙ ከዛሬ ጀምሮ በባህር ዳር ከተማ ይካሄዳል


ገጽ 4




## ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የኅብረተሰቡን ባህል ማሳደግ ይገባል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በባህልና ቋንቋ ላይ ትኩረት በማድረግ እየሠራ መሆኑን


ማህበራዊና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ደመቀ መኮንን የሶማሊያውን ጠቅላይ ሚኒስትር በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋገረዋል

## “የኢትዮጵያና የሶማሊያ ግንኙነት ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ ነው”

-ሀምዛ አብዲ ባሬ
የሶማሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር

አብዱረዛቅ መሐመድ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ እና የሶማሊያ ግንኙነት ልክ እንደ አንድ ቤተሰብ የጠነከረና ለዘመናት የተሻገረ መሆኑን የሶማሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ገለጹ:: ሶማሊያውያን ፈተና በገጠማቸው ጊዜ ሁሉ ኢትዮጵያውያን ከጎናቸው በመሆናቸውም ምስጋና አቅርበዋል::

የሶማሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሀምዛ አብዲ ባሬ ከነገ ጀምሮ በባህር ዳር ከተማ በሚካሄደው የጣና ፎረም ላይ ለመሳተፍ ትናንት አዲስ አበባ በገቡበት


“የኢትዮጵያና የሶማሊያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## ከተማ አስተዳደሩ ለመከላከያ ሠራዊት ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ




ገጽ 3



# አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም መነገዱን እንዲያቆም የትግራይ ተወላጆች አሳሰቡ

**ጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም መነገዱን እንዲያቆም በዲላና በደሴ ከተሞች የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች አሳሰቡ፡፡ በከተሞቹ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ውይይት አካሂደዋል፡፡

በዲላ ከተማ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ትናንት በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ ባካሄዱት ውይይት እንደገለጹት፤ ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም እየነገደ የስልጣን ጊዜውን ለማራዘም እንጂ ለሕዝቡ አስቦ አያውቅም፡፡

አሸባሪው ሕወሓት መንግሥት ያቀረበውን የሰላም ጥሪ ወደ ጎን በመተው ለ3ኛ ጊዜ ጦርነት መክፈቱን ያወገዙት ነዋሪዎቹ፤ በድርጊቱ ማዘናቸውንም ገልጸዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት ሰላም፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በሰላም መኖር ሆኖ ሳለ ክልሉን ለብቻው አፍኖ ለእኩይ ዓላማ ማዋል የአሸባሪው ሕወሓት የከሰረ ፖሊቲካ ቁማር እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ድርጊቱን በመላ ዓለም የሚኖር የትግራይ ተወላጆችም ሆኑ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሊያወግዙት እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

መንግሥት የትግራይ ሕዝብ ጠላት የሆነውን አሸባሪውን የሕወሓት ቡድን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እንደሚደግፉ በመግለፅ፣ ማንኛውም እኩይ ተግባር ላይ የተሰማራን አሸባሪ አካል ለሕግ አሳልፎ መስጠት እንደሚገባ መናገራቸውን የጌዴኦ ዞን ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ሕዝብ ግንኙነት መረጃ ያመለክታል።

በተመሳሳይ ዜናም በደሴ ከተማ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ላይ ትናንት ውይይት አድርገዋል። በውይይቱም አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ አሸባሪው ቡድን በሚያራምደው አቋም የትግራይ ሕዝብና ሕፃናት እየተጎዱ እንደሆነ አንስተው፤ ይህ አካሄድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ መንግሥት የሚያቀርበውን ማንኛውንም ጥሪ ተቀብለው እንደሚተገብሩ ገልፀዋል።

አገር ለማፍረስ የተሠማራ ማንኛውም አካል ጋር እንደማይተባበሩ በዚህ ሂደት ውስጥ አሸባሪው ሕወሓትን በመደገፍ የተሰማሩ የትግራይ ተወላጆች ካሉ ከእኩይ ድርጊታቸው እንዲታቀቡም አሳስበዋል።

የአሸባሪውን ትህነግ እኩይ ተግባር ለማውገዝ ከመድረክ ባለፈ በአደባባይ በሰላማዊ ሰልፍ እንድናወግዝ ከተማ አስተዳደሩ እንዲፈቅድልን ሲሉ ደሴ ከተማ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ጥያቄ አቅርበዋል።

በውይይቱ ላይ የተገኙት የደሴ ከተማ አስተዳደር ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ አቶ ሳሙኤል ሞላልኝ እንደገለጹት፤ የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች ልጆቻቸውን በአውሮፓና በአሜሪካ በድሎት እያኖሩ ደሀውን የትግራይ ሕዝብ ከሕፃን እስከ አዋቂ ወደጦርነት እየማገዱ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በከተማችን የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ይሄን አሸባሪ ድርጅት በግልጽ ማውገዝ እንደሚገባና የትግራይን ሕዝብ ከሕወሓት የሰቆቃ አገዛዝ ለማላቀቅ በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት እንዳለባቸውም ማሳሰባቸውን የደሴ ከተማ ኮሙዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ዘግቧል።

# ስልጠናው በሕፃናት አያያዝና እንክብካቤ ላይ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ለመቅረፍ ያስችላል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- የሕፃናት አያያዝና እንክብካቤ ላይ የተሰጠው ስልጠና የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ለመለየትና ለመቅረፍ ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሕፃናትን በአዕምሮና በሥነ ልቦና ብቁ አድርጎ ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስልጠና ከአዲስ አበባ እና ከሁለት ክልሎች ለተውጣጡ 300 ባለድርሻ አካላት ተሰጥቷል፡፡

ትናንት በሂልተን ሆቴል በተካሄደው ሥልጠና ላይ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደገለጸው፤ ስልጠናውን ያዘጋጀው ኦል ጋድስ ችልድረን ኢንተርናሽናል ግብረ ሰናይ ድርጅት አሜሪካ ቴክሳስ ከሚገኘው ከረን ፐርቪስ ሕፃናት ተቋም ጋር በመተባበር ነው፡፡

በሥልጠና መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ አማካሪ ዶክተር ዘርሁን ከበደ እንደገለጹት፤ ሕፃናትን መጠበቅ መንከባከብ በአካል በአዕምሮአቸውና በሥነ ልቦናቸው ብቁ አድርጎ ማሳደግ በምድር ላይ ያለውን የሰው ልጅ ዘር ማስቀጠል ነው፡፡



ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሕፃናት በአካል፣ በሥነ ልቦናቸውና በማህበራዊ ጉዳዮች ሁለንተናዊ ስብዕና ይዘው እንዲያድጉ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ተባብሮ በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

ሥልጠናው ወላጆች ከዕውቀት ማነስ የተነሳ ሕፃናት በዕድላቸው ያድጋሉ በሚል በተሳሳተ አስተሳሰብ በምግብ ዕጥረት መቀንጨር፣ ልብስና መጠለያ ማጣት፣ በግጭቶች ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናት ለመታደግ አቅም ይፈጥራልም ተብሏል፡፡

የሕፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ ፣ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ኅብረተሰቡ እንዲከላከል ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በትኩረት በመሥራት ላይ ይገኛል ያሉት ዶክተር ዘሪሁን፤ ኦል ጋድስ ችልድረን ኢንተርናሽናል ግብረ ሰናይ ድርጅትም ከዚህ አንጻር የሚሰጠው የስልጠና ድጋፍ ለሕፃናት ሁለንተናዊ መብቶችና ጥቅሞች መረጋገጥ ትልቅ አቅም ይፈጥራል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሕፃናት ላይ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ከድህነት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ከዚህ ለማላቀቅ የኢኮኖሚ ችግሮች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦል ጋድስ ችልድረን ኢንተርናሽናል ግብረ ሰናይ ድርጅት ዳይሬክተር አቶ ማቴዮስ ሻሞ በበኩላቸው ስልጠናው በመተማመን ላይ በተመሠረተ የሕፃናትን ሁለንተናዊ መብቶችና ጥቅሞችን ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ ሕፃናትን በአንድ ማዕከል በመሰብሰብ አስፈላጊውን ሥልጠና በመስጠት ቤተሰቦቻቸውን እንዲቀላቀሉ መደረጉን ጠቅሰው፣ በጦርነት ቀጣና ለሚገኙ ሕፃናት የሚሆን ግማሽ ሚሊዮን ብር የሚሆን እገዛ ተደርጓል ብለዋል፡፡ የሥልጠና ፕሮግራሙ ወደ ሁሉም ክልሎች እንደሚሰፋ ገልጸዋል፡፡

በአፍሪካ ኦል ጋድስ ችልድረን ኢንተርናሽናል ዳይሬክተር አንጄሊ ሳሌር ድርጅቱ በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ለመቀነስ የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም ለመፍጠር ለ30 ዓመታት ልምድ ያለው ተቋም መሆኑን ጠቅሰው፣ በአስር አገራት ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ስልጠናው ከኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ እና ከጋምቤላ ለተውጣጡ 300 ባለድርሻ አካላት ለሁለት ቀናት እንደሚሰጥ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# በቀጣዮቹ አስር ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ ለእርሻ ሥራ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዮቹ አስር ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተከናወነ ለሚገኘው የእርሻ ሥራ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

ኢንስቲትዩት እኤአ ከኦክቶበር 11 እስከ 20 ቀን 2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽእኖ አስመልክቶ ለዝግጅት ክፍላችን በላከው የትንበያ መረጃ እንዳስታወቀው፤ በቀጣዮቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል። ይህም በተለይም በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል ብሏል።

ከሚጠናከሩ ሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተነሳ በአንዳንድ የምዕራብና የደቡባዊ የአገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚጠበቅ ያስታወቀው የኢንስቲትዩቱ ትንበያ፤ ይህም ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አመላክቷል፡፡

በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙና ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የእርጥበት ፍላጎት ከማረጋገጥ አንጻር አወንታዊ ሚና እንዳለውም የኢንስቲትዩቱ መረጃ ያሳያል፡፡

በመጠን አነስተኛ ቢሆንም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ወደ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሚኖረው መስፋፋት ለደጋማ አካባቢዎች የማሣ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጠር የተጠቆመ ሲሆን፤ በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚፈጠር መጠቀም እንደሚገባ ያስታወሰው መግለጫው፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የደረሱ ሰብሎች ስብሰባ እየተከናወነ ስለሆነ እርጥበት የሚጠበቅባቸው አካባቢዎች እርጥበቱ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉም አሳስቧል፡፡

በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የአገሪቱ ክፍል የሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል አመልክቶ፤ በአብዛኛው የባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ዓባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አሞጊቤና ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች እርጥበታማ መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል ብሏል የኢንስቲትዩቱ ትንበያ፡፡

# ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኩ ገብተው እንዲያስሙ ጥሪ ቀረበ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በፋርማሲቲካል ዘርፍ የተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው እንዲያለሙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጥሪ አቀረበ። በፋርማሲቲካል ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክን የጎበኙ ሲሆን፣ በፓርኩ ስላለው ምቹ ሁኔታ ገለጻ ተደርጎላቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የማርኬቲንግና የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ሄኖክ አስራት ለባለሀብቶች እንደገለጹት፤ በፋርማሲቲካል ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች በፓርኩ ኢንቨስትመንት እንዲያደርጉ ያለውን ምቹ ሁኔታ አብራርተዋል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በአገራቸው ኢንቨስት በማድረግ ራሳቸውን ለውጠው አገራቸውን የሚለውጡበትን መንገድ ኮርፖሬሽኑ እያመቻቸ ነው።

የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ኮርፖሬሽኑ በሚችለው አቅም ሁሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ያደርጋል ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በግልም ሆነ በጋራ በመሆን የሚያለሙበት መንገድ ይመቻቻል ብለዋል። ፓርኮቹ ዓለም ላይ ያሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሟሉትን መሠረት ልማት ሁሉ ያሟሉ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሄኖክ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር በየአመቱ በ2 ነጥብ 3 ያድጋል። በዚህም በጤናው ዘርፍ የመድኃኒት ፍላጎት እያደገ ይመጣል። ለዚህም የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ኢንቨስት ቢያደርጉ ውጤታማ ይሆናሉ።

ባለሀብቶቹ በኢንዱስትሪው ኢንቨስት ቢያደርጉ የታክስ የክፍያ የእፎይታ ጊዜ፣ ከውጭ ለሚያስገቧቸው ግብአቶች ድጋፍ፣ የውርስ ዋስትና እንደሚሰጥ ያብራሩት አቶ ሄኖክ፣ የሊዝ ዋጋው በካሬ ሦስት ነጥብ 73 ዶላር በአመት እንደሆነና ምርታቸውን ወደ ውጭ ሲልኩ ከታክስ ክፍያ ነፃ የማድረግና የገንዘብ ነክ ማበረታቻ እንዳለ ገልጸዋል።

የቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሥራ አስኪያጅ አቶ መንግሥቱ ረጋሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ቂሊንጦ ኢንዱስትሪያል ፓርክ መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት ሲሆን፣ እስካሁን በፓርኩ 17 ባለሀብቶች ገብተው እያለሙ ነው።

ባለብቶቹ በፓርኩ ሲገቡ በፈለጉት ዲዛይን በመገንባት ነው ያሉት አቶ ሄኖክ፤ ካለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ወደ ፓርኩ የሚመጣው የኢንቨስትመንት ጥያቄ ከፍተኛ ነው ብለዋል። ወደ ፓርኩ የገባ ኢንቨስተር ተደስቶና ኢንቨስት የማድረግ ፍላጎቱ ጨምሮ እንደሚመለስም ጠቁመዋል።

ባለሀብቶች የመሬት ሊዝ ዋጋው በዶላር መሆኑ አሁን ባለው የምንዛሬ ዋጋ ጭማሬ ያስቸግራል። ስለዚህ የሊዝ ዋጋው በኢትዮጵያ ብር ቢሆን መልካም ነው ሲሉም አስተያየታቸው ሰጥተዋል።

በኢንዱስትሪው ያሉ መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ዓለም ላይ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሟሉትን መሠረት ያደረገ መሆኑን አቶ ሄኖክ ተናግረው፤ የሊዝ ዋጋው በዶላር ስሌት በብር የሚከፈልበት መንገድ እየተመቻቸ ስለመሆኑም ገለጻ ተደርጎላቸዋል።

በኢትዮጵያ 13 ኢንዱስትሪ ፓርኮች የተገነቡ ሲሆን 125 ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል። በዚህም ባለፈው አመት ብቻ ከ932 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል። ከ81 ሺህ በላይ ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

# ከተማ አስተዳደሩ ለመከላከያ ሠራዊት ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ፎቶ:- በሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት ከ30 ሚሊዮን 249 ሺህ 978 ብር በላይ የዓይነት ድጋፍ አደረገ። አስተዳደሩ እስከ አሁን ከ214 ሚሊዮን ብር በላይ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

ከተማ አስተዳደሩ ያደረገው ድጋፍ ለ4ኛ ዙር ሲሆን፣ ሁሉንም ክፍለ ከተሞችን በማሳተፍ ነው። በዚህም 477 ሰንጋዎች፣ 319 ኩንታል ደረቅ ምግብ፣ 2 ሺህ 30 ሊትር ዘይት፣ ፍራሾች፣ አልባሳት እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስን ጨምሮ ሌሎች ለሠራዊቱ የሚውሉ ድጋፎችን በማሰባሰብ አስረክቧል።

ድጋፉን በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የፋይናንስ ኃላፊ ወይዘሮ ነጂባ አክመል ለመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሊዊጂ ሲያስረክቡ እንደተናገሩት፤ አስተዳደሩ ለመከላከያ ሠራዊት ድጋፍ ሲያደርግ ለ4ኛ ጊዜ ሲሆን፣ በመጀመሪያ፣ በ2ኛ እና በ3ኛ ዙር ከ214 ሚሊዮን 364 ሺህ 943 ብር በላይ የሚገመት የዓይነት ድጋፍ ማድረጉን አስታውሰዋል።

ድጋፉን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከከተማው መስተዳድር ጋር በጋራ አስረክበዋል ያሉት ወይዘሮ ነጂባ፣ የመከላከያ ሠራዊቱ የኢትዮጵያን ህልውና ለማስጠበቅና አሸባሪው ቡድን የከፈተውን ጦርነት ለመቀልበስ በሚያደርገው ተጋድሎ በስንቅና በሞራል በመደገፍ ደጀንነታችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

መከላከያ አሸናፊ የሚሆነው የሕዝብ ደጀንነቱ ተጠናክሮ ሲቀጥል መሆኑን የተናገሩት ኃላፊዋ፣ እስካሁን ሠራዊቱ ከሕዝብ ድጋፍ አልተለየውም። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ድጋፍም ሠራዊቱን ይበልጥ እንደሚያበረታታውና አገር ለማፍረስ እያሴሩ ያሉ የሽብር ቡድኖች በአጭር ጊዜ እንደሚጠፉም ተናግረዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሊዊጂ ለተደረገው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠራዊቱን በመደገፍ እያደረገው ያለውን ርብርብ በየተሰማራባቸው መስኮች በመድገም ለአገር ሠላም መከበር የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

የተፎካካሪ ፓርቲ የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ሙልጌታ አበበ በበኩላቸው፣ ሁለት ሀሳብ እንጂ ሁለት አገር የለንም፤ አገርን ለሚጠብቀው ሠራዊታችን ድጋፋችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

ይሄ ድጋፍ በዋናነትም የሠራዊታችንና ጥምር ጦሩ እያደረገ ላለው እንቅስቃሴ ከጎናችሁ ነን፤ አይዟችሁ ጠንክሩ፣ በርቱ ለማለትና ለሠራዊቱ ደጀን መሆናችንን ለማረጋገጥ ነው እዚህ የተገኘነው ብለዋል።

# የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሠራታቸው በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ነው

**ማህሌት አብዱል**

አዳማ፡- በአገሪቱ የሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራዎች በቅንጅት ባለመሠራታቸው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ ተገለጸ። ጉዳቱን ለመከላከልም ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ተገለፀ።

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ትብብር በአዳማ ከተማ በተዘጋጀው የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አገር አቀፍ ጉባኤ ላይ እንደተገለፀው፤ ባለፈው በጀት ዓመት ለመሠረተ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ቢሰጥም ተቋማት ተቀናጅተውና ተናበው የመሥራት ባህላቸውን አሁንም በሚገባው ልክ ማሳደግ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ትናንት ጉባኤውን ሲከፍቱ እንደተናገሩት፤ ባለፉት ዓመታት መንግሥት በአገር ደረጃ ለመሠረተ ልማት ዝርጋታ ትልቅ ትኩረት በመስጠቱ አገሪቱ አመርቂ እና ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ነው። ይሁንና በተመሳሳይ መልኩ ለመሠረተ ልማት ሥራ ቅንጅትና እና ትብብር የግንባታውን ያህል በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ ከዘርፉ መጠቀም ባለባት መጠን መጠቀም ሳትችል ቆይታለች። በተለይም የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሠራታቸው ምክንያት ዘርፉ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍለቂያ መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል።

‹‹መሠረተ ልማት የአንድ አገር እድገት ወሳኝ ግብዓትና ውጤት ነው። ለዚህም በአገራችን ከፍተኛ በጀት በመመደብ ለመሠረተ ልማት ግንባታውም ሆነ የጥገና ሥራዎች ቅንጅትና መናበብ በመጉደሉ ምክንያት ከፍተኛ የሀብትና የጊዜ ብክነት ይታይበታል›› ያሉት ሚኒስትሯ፤ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት የመሠረተ ልማት ገንቢ ተቋማት የሚታየውን የቅንጅት ክፍተት ማረም እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል። በተጨማሪም ተቋማቱ በተናበበ መልኩ ወደ ተሻለ አሠራር በመግባት ዘርፉ የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ እንዳይሆን በቅንጅት መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አመልክተዋል።

እንደሚኒስትሯ ገለፃ፤ ቅንጅቱን ለማረጋገጥ የሕግ ማዕቀፍ እና መዋቅር የመፍጠር ሥራ የተሠራ ቢሆንም የሚናበብ የተቀናጀ ፕላንና ስታንዳርድ አለመኖር፣ የመሠረተ ልማት መረጃ አለመደራጀት፣ ተቋማዊ ባህል በሚናበብና በተቀናጀ ሁኔታ መሥራት ያለመቻሉ፣ ተቋማዊ አቅም ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም የሕግና አሠራር ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመሟላት በዘርፉ



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

ተጨባጭ ለውጥ እንዳይመጣ አድርጓል።

በመሆኑም የመሠረተ ልማት ሥራዎችን በማቀናጀትና በማስተባበር አገራዊ የቅንጅት ማስተር ፕላን ማዘጋጀት፣ ወጥ የሆነ የካሳ አሠራር እንዲኖር ማድረግ እንደሚገባም ወይዘሮ ጫልቱ ተናግረዋል። በተለይም የአካባቢው የነጠላ ዋጋ ሰነድ ማዘጋጀት፣ የመሠረተ ልማት ሥራዎች በሚተገበሩበት ወቅት አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በመቀነስ፣ ኮድና ስታንዳርድ በማዘጋጀትና በመተግበር እንዲሁም የተሟላና የተደራጀ መረጃ ማዕከል እንዲኖር መሥራት ይጠበቃልም ብለዋል።

‹‹ለእድገት አስፈላጊ መሠረተ ልማትና አገልግሎት በተለይ መብት ኃይል፣ መንገድና ውሃና ፍሳሽ እንዲሁም ትራንስፖርት በበቂ ሁኔታ እንዲቀርቡ ማስቻል ይገባል›› በማለት ተናግረው፤ ለዚህም የሁሉንም ሚና በማጎልበትና የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮችን በማስፋት የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን ተደራሽነትን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የአገራዊ የተቀናጀ መሠረተ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቴዎድሮስ ተገኝም የመሠረተ ልማት ቅንጅት እና ትብብር የግንባታውን ያህል በቂ ትኩረት አለማግኘቱን ይስማማሉ። በዚህም ምክንያት አንዱ የመሠረተ ልማት ተቋም የገነባውን ሌላው ተቋም ማፍረስ፣ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት አለመጠናቀቅ ችግር በስፋት እንደሚስተዋል አመልክተዋል።

የቅንጅት ችግሩ የኅብረተሰብ የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ በመሆን አገሪቱ ከዘርፉ መጠቀም ያለባትን ያህል መጠቀም ሳትችል መቆየቷን ተናግረዋል። አክለውም ‹‹በአንዳንድ ፕሮጀክቶች በቅንጅት ማነስ እና በሌሎች ምክንያቶች የፕሮጀክት ወጪ መናር እና የጊዜ ማጓተት ይስተዋላሉ›› ብለዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በአገሪቱ እየተፈጠረ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በአግባቡ ለመምራት የተቀናጀ መሠረተ ልማት ሥራችዎችን አሁን ከተደረሰበት የዕድገት ደረጃ ለማሳደግ አማራጮችን ማስፋትና ማጠናከር ይገባል። በዋናነትም ቅንጅታዊ አሠራሩን ማዘመን፣ ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ያለው የሰው ኃይል መፍጠር፣ የሕዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ናቸው።

በዚህ ረገድ ባለፈው በጀት ዓመት በሰሜንና በምዕራቡ የአገሪቱ ክፍሎች ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት የፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ በመቀዛቀዙ ከዕቅድ አንጻር መፈጸም አለመቻሉን አቶ ቴዎድሮስ አመልክተዋል። በተቋማት ሪፎርም ምክንያት ሥራዎች በሚፈለገው ልክ አለመሄዳቸውን ጠቁመው፤ አስፈፃሚ ተቋማት ለቅንጅት ሥራው ትኩረት አለመስጠትና ችግሮች ሲፈጠሩ በጋራ ለመፍታት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ለአፈፃፀሙ ማነስ አብይ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አንስተዋል።

በዚህ ረገድ በአገር አቀፍ ደረጃ ተናቦ የመሥራት ባህሉን ለማዳበር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በመሠረተ ልማት ሥራዎች ምክንያት ለሚነሱ ንብረቶች በአንድ አካባቢ ለተመሳሳይ ንብረት የተለያየ የካሳ ክፍያ መፈጸም፣ በነባር የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች በቅንጅት እጦት ይደርስ የነበረውን ጉዳት ለመቀነስ ከፈጻሚ ተቋማት ጋር የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በጋራ መስክ ድረስ በመውረድ ለተፈጠሩ ችግሮች በመወያየት መፍትሄ መስጠት መቻሉን አስረድተዋል።

ይሁንና በቅንጅት እጦት ምክንያት እየደረሰ ያለውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ በተፈለገው ልክ ለውጥ ማምጣት ያለመቻሉን አመልክተዋል። በተለይም የተቀናጀ መሠረተልማቶች መረጃ አስተዳደር መገንባትና ለመሠረተልማት ፕሮጀክቶች የቅንጅት ፈቃድ መስጠት አለመቻሉ፤ አገራዊ ማስተር ፕላን የቅድመ ዝግጅት ሥራ አለመጠናቀቃቸውና አስገዳጅ የመሠረተ ልማት ቅንጅት ሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ አብይ ምክንያቶች እንደነበሩ አስገንዝበዋል።

ለአምስት ቀናት በአዳማ ከተማ እየተካሄደ ባለው የተቀናጀ መሠረተ ልማት አገር አቀፍ ጉባኤ የፌዴራል፤ የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ዜና

# 10ኛው የጣና ፎረም የሰላምና ደህንነት ጉዳዮችን በተመለከተ የዜጎች ሚና ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይመክራል

## -ፎረሙ ከዛሬ ጀምሮ በባህር ዳር ከተማ ይካሄዳል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- 10ኛው የጣና ፎረም ከዛሬ ጀምሮ በባህርዳር ከተማ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮችን በተመለከተ የዜጎች ሚና ላይ ትኩረቱን አድርጎ እንደሚካሄድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ትናንት በወቅታዊ ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ 10ኛው የጣና ከፍተኛ ፎረም የሠላም፣ የደህንነትና የጸጥታ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ይካሄዳል።

ሰላምና ጸጥታን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ከመንግሥታት ሚና ባለፈ ዜጎች የሚኖራቸው ሚና ላይ ትኩረት አድርጎ ይመክራል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ፎረሙን ስኬታማ ለማድረግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የአማራ ክልልና ዓለም አቀፍ የደህንነት ተቋማት ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊው ሁሉ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ ፎረሙ በተለይም በአፍሪካ የሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ የአፍሪካን ሰላምና መረጋጋት የሚያውኩ ጉዳዮች ተነስተው ይመከርባቸዋል፤ ምክረ ሀሳቦችም ይቀርቡበታል። እንዲሁም ፎረሙ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ግጭትን የመቋቋም አቅምን እንዴት መቋቋም ይቻላል በሚል ሀሳብ ላይ ይመክራል። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በዓለም ጠቀሜታው እየጨመረ በመጣው የአረንጓዴ አሻራ ሂደት፣ ጠቀሜታና ስኬት ላይም ውይይት ይደረጋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ዓለምን እየፈተናት ያለው የአየር ንብረት ለውጥ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ ፖለቲካና ዲፕሎማሲ በመሆኑ የአረንጓዴ አሻራ በኢትዮጵያ ብቻ ቢወሰን የሚኖረው ተጽዕኖ እምብዛም ስለሚሆን በሌሎች የጎረቤት አገሮች አረንጓዴ አሻራን የማስፋት ሥራ ይከናወናል። የአረንጓዴ አሻራ ዲፕሎማሲ ተብሎ ሊጠራም ይችላል ብለዋል።

የአረንጓዴ ዲፕሎማሲን ከሌሎች የጎረቤት አገሮች ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ተጀምሯል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ አገራችን በዚህ መስክ ለመተሳሰር የሚያስችል የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብርን ከጥቅምት ሦስት እስከ 22 ቀን 2015 ዓ.ም በስድስት የአፍሪካ አገሮች ታካሂዳለች ሲሉም ተናግረዋል። መርሃግብሩም በደቡብ ሱዳን ዋና ከተማ ጁባ ጀምሮ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ሩዋንዳ፣ ኬንያና ጅቡቲ የሚካሄድ ይሆናል ብለዋል።

ለአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ወደ ጎረቤት አገሮች የሚሄዱ ወጣቶችን የአሸኛኘት ሥነሥርዓት ጥቅምት አንድ ቀን 2015 ዓ.ም መደረጉን የገለጹት ቃል አቀባዩ፤ የአረንጓዴ አሻራ መርሀግብርን እሴት ለጎረቤት አፍሪካውያን ለማካፈል ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተውጣጡ ወጣቶች ወደ ጎረቤት አገራት ማቅናታቸውን ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ ኢትዮጵያውያን በጎረቤት አገራት በሚኖራቸው ቆይታ የአረንጓዴ አሻራ ተሞክሮን ከማካፈል ባሻገር ከየአገራቱ ወጣት አቻዎቻቸው ጋር ልምድ የሚለዋወጡባቸውና የሚመካከሩባቸው መርሀግብሮች ይኖራሉ።

የተቋማትና የአገራት መሪዎችን ጨምሮ 300 የሚሆኑ ተሳታፊዎች ይሳተፋሉ ተብሎ በሚጠበቀው ጉባዔ የአፍሪካን ግጭት የመቋቋም አቅም እንደሚገመገምም አምባሳደሩ ገልጸዋል።

# በ2014 ዓ.ም 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ቤቶች ከፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን የሚሆኑ ቤቶች ከፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ መሆናቸውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሐብታሙ ኢተፋ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በተለያዩ አካባቢዎች ከዋናው የኤሌክትሪክ መሥመር ውጪ ያሉ (የኦፍ ግሪድ) የተሰሩ የፀሐይ ኃይል ማመንጫዎች በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ቤቶችን ተጠቃሚ አድርገዋል፡፡

ከኦፍ ግሪድ የፀሐይ ኃይል ማመንጫዎቹ በተጨማሪ የቤት ለቤት የፀሐይ ኃይል ቁሶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ ሥራ በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመትም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የ2014 ዓ.ም በተለይ በኢነርጂው ዘርፍ ትልቅ የማምረት አቅም የተፈጠረበት ዓመት መሆኑን የጠቁመው ሚኒስቴሩ፤ ሆኖም እምርታ እየታየበት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ሊያዳርሳቸው የማይችላቸው የተንጠባጠቡ መንደሮችን የፀሐይ ኃይል እንደ አማራጭ እንደሚወሰድም ገልፀዋል፡፡

እስካሁን በተጠኑ ጥናቶችና ባለው ነባራዊ ዕውነታ በአገሪቱ ያሉ የኢነርጂ ምንጮች የመጀመሪያው ውሃ ቀጥሎ ደግሞ የፀሐይ ኃይል ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ከውሃ የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማሳደግ ከምታደርገው ጥረት ጎን ለጎን ሶላር ኢነርጂን በመጠቀም የሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይልን ከፍ ለማድረግ እየሠራች የምትገኘው ሥራ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት ኅብረተሰቡ በመንግሥት በኩልና በግሉ ከሚያገኛቸው የፀሐይ ኃይል አገልግሎቶች በተጨማሪ በተበታተነ መልኩ ያሉ መንደሮችን ለማገልገል የተገነቡ የውሃ ተቋማት ከሚጠቀሙት ጀነሬተር ኃይል በፀሐይ ኃይል በሚሠሩ ኢነርጂዎች እንዲጠቀሙ እንደሚደረግም ገልፀዋል፡፡

ኅብረተሰቡ በግሉ የፀሐይ ኃይልን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚቀይሩ መሣሪያዎችን መጠቀም መጀመሩ የሚበረታታ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ኢንጅነር ሐብታሙ፤ መንግሥት ይህንን ለመደገፍ በአግባቡ የማይሠሩና ደረጃቸውን ያልጠበቁ የሶላር ኢነርጂ መሣሪያዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በትኩረት መሥራቱንም ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን የተበታተኑ መንደሮችን ከዋናው የኤሌክትሪክ መሥመር ውጭ በሆነ መንገድ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ በ2015 ዓ.ም አነስተኛ የሆኑ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ዲዛይን ማድረግ ላይ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

በተለይ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል ብዙ ወንዞች መኖራቸውን የጠቆሙት ሚኒስትሩ ፤ ወንዞቹን ለኃይል ማመንጫነት በመጠቀም ዜጎችን የኢነርጂ ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

ዶክተር ኢንጅነር ሐብታሙ፣ አገሪቱ ካላት ወንዞች አብዛኞቹ ያሉበት ተፋሰስ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ምቹ መሆናቸው መረጋገጡንና በትናንሽ ወንዞች እንኳ ብዙ የኃይል እጥረቶች መፍታት እንደሚቻልም አብራርተዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በባዮጋዝ አጠቃቀም ረገድም ኅብረተሰቡ ግንዛቤ አግኝቶ እንዲጠቀም ለማስቻል ጥረት መደረጉን ያነሱት ሚኒስትሩ፣ በዚህም ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በዘርፉ በመቀላቀል ተጠቃሚ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ ጥረቱ በተያዘው በጀት ዓመትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል፡፡

## አዲስ የሥራ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

እየሠራችሁ ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ይቀርብልናል ሲሉ ያስታውሳሉ።

ለእነዚህ ጥያቄዎች ዋናው መልስ በሶማሌ ክልል መንግሥት ባለፈው ዓመት የተጀመረውና በሚቀጥሉት ዓመታት ተስፋፍቶ መቀጠል ያለበት የስንዴ ልማት ሥራ መሆኑን በመግለጽ፤ በአገራችን እየታየ ያለውን የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ማርገብ የሚቻለው በዚሁ የስንዴ ልማት መሆኑንም ጠቅሰዋል። የስንዴ ልማቱም እየተሠራ ያለው ድርቅንና በምግብ ራስን ለመቻል ብቻ ሳይሆን የዋጋ ንረትን የሚቆጣጠር ስለሆነም ጭምር ነው ባይ ናቸው።

ባለፈው ዓመት በሱማሌ ክልል 847 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ልማት መሸፈኑን የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ይህም በክልሉ ሊለማ ከሚችለው መሬት 10 በመቶ ብቻ ነው። በዘንድሮ ዓመት ደግሞ የሚለማውን መሬት ለመጨመርና ምርታማነትን ለማሳደግ ዝግጅት አድርገናል። አገራችን ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በያዘችው ዕቅድም ክልሉ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጅት ላይ ይገኛል ብለዋል።

በሦስት ወንዞች የበይና የመስኖ መሠረተ ልማቶችን የመዘርጋት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አመልክተው፤ ለውሃ ማቆርና መስኖ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ከተሠራው እጥፍ መሥራት ታቅዷል ብለዋል። ለዚህም የሶማሌ ክልል ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

ሶማሌ ክልል ውስጥ በሄክታር ከ40 ኩንታል በላይ ስንዴ የሚገኝበት ማሳ ማየት የዓምናውን ድርቅና ችግር ላየ ሰው ይህ የስንዴ ልማት ተዓምር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ በአሁኑ ጊዜ አመራር እየሰጠን ያለን ሰዎች የምንናገርና የምንጀምር ብቻ ሳይሆን የምንጨርስና ቃላችንን በተግባር የምናሳይ መሆናችንን ሕዝብ እየተገነዘበ መጥቷል ነው ያሉት።

በበጋ ስንዴም የምናመርተው ምርት ከዓምናው እጥፍ መሆን አለበት። የሶማሌ ክልል ባለፈው ክረምት በሠራው ሥራ ቢያንስ ከስድስት እስከ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል እንደሚያመርት ይጠበቃል። በርሃውን ለም ካደረጉ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ለዓለም ገበያ የሚቀርብ ስንዴ ማምረት አይከብዳቸውም። ይህንንም ይተገብሩታል ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

## ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2014 ዓ.ም ስኬታማ ሥራዎች መሥራቱን ገልጿል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፈው በጀት ዓመት በባህልና በቋንቋ ዘርፍ የኅብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን የሠራ ሲሆን በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት በተቀመጡ ትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በማተኮር ይበልጥ ለመሥራት እየተንቀሳቀሰ ነው።

ባህልና ቋንቋ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት ከማጠናከር በዘለለ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በእደጥበብና በኪነጥበብ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የቋንቋ ፖሊሲ ዝግጅት፣ ትርጉምና አስተርጓሚነት፣ ፊደላት፣ ሥነ ቃልና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ጥናትና ምርምሮች ተሰርተዋል። የቋንቋ ጥናት ማዕከል ለመገንባት ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው ሲሉም አያይዘው ገልጸዋል።

ስፖርትን በማሳደግ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል። በተሠሩ ሥራዎችም በዓለም አቀፍ መድረኮች በኮሎምቢያና በሆሪገን በተካሄደው የአትሌቲክስ ውድድር ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል። እደጥበብ ሥራዎችን በማጠናከር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን ለማሳለጥ የሚያግዝ የእደጥበብ ማዕከል ግንባታ ለማካሄድ ውል በማደስ ወደሥራ መገባቱን ገልጸዋል ።

በአገር ግንባታ ውስጥ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ እሴቶች ድርሻ ትልቅ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ባህልን በማሳደግ ረገድ የአደባባይ በዓላትን በጥሩ ሁኔታ ማክበር ተችሏል። ወደ ተለያዩ ክልሎች በመጓዝ እሴቶታቸውን የሚያንጸባርቁ የተለያዩ በዓላትን በአንድነት ማክበር ተችሏል ብለዋል።

የ2015 ዓ.ም የትኩረት አቅጣጫዎች ባህል ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ገልጸዋል። ይህንን ሥራ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ በእደጥበብ ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችና ተቋማትን በማጠናከር፣ ቴክኒካዊና ሙያዊ እገዛ በማድረግ በማስተዋወቅና በመሸለም ከትኩረት አቅጣጫዎች እንደምሳሌነት አንስተዋል። ለስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቁ የስፖርት ሜዳ እና ትናንሽ ስፖርት ሜዳዎችን በክልሎችና በቀበሌ ደረጃ መገንባት ሌላኛው ትኩረት አቅጣጫ ነው ብለዋል።

መጀመሪያና ሁለተኛ ዙር ስፖርት ሜዳዎች ግንባታ በቻይና ኮንትራክተር የተያዘው ስታዲየም ግንባታ መዘገየቱ ትልቁ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማነቆ መሆናቸውን ገልጸው፣ ኮንትራክተሮቹ ያቀረቡትን የዶላር ችግር ለመፍታት ተሞክሯል ብለዋል። ሆኖም ግን ምክንያት በመደርደር በማጓተት ላይ ስለሚገኙ እርምጃ ወደ መውሰድ እየተገባ መሆኑን ገልጸዋል።

የባህልና የስፖርት ሥራ የሕዝብ ሥራ ነው ያሉት አቶ ቀጄላ በቅድሚያ የሚኒስቴሩን መስሪያ ቤት የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎች ተጠናክሮ መሠራት አለበት። በመቀጠልም ሚዲያዎችም የኅብረተሰቡን ባህልና ቋንቋ የሚያጠናክሩ ሥራዎችን በመሥራት በሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርበዋል።

## “የኢትዮጵያና የሶማሊያ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ወቅት የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በጽሕፈት ቤታቸው የተቀበሏቸው ሲሆን፣ በሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ዙሪያም ተወያይተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ሀምዛ አብዲ በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት፤ ሶማሊያውያን ችግር በገጠማቸው ጊዜ ሁሉ ኢትዮጵያውያን እህት ወንድሞቻቸው ከጎናቸው እንደነበሩ አስታውሰው፤ የሁለቱ አገራት ግንኙነት የአንድ ቤተሰብ ግንኙነት እንደሆነ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁንም ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በሚደረገው ጥረት የሁለቱ አገራት ሕዝቦች በጋራ እንዲቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ላላት ግንኙነት ልዩ ትኩረት እንደምትሰጥ የገለጹ ሲሆን፤ የሁለቱ አገራት ሕዝቦች በመልክዓ-ምድር፣ በባህል፣ በንግድ፣ በታሪክና በሌሎችም ጉዳዮች የተሳሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ይህንን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉም አቶ ደመቀ መኮንን አብራርተዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ጉብኝት የሁለቱን አገራት የቆየ ወዳጅነት ይበልጥ ለማጎልበት ዕድል የሚፈጥር ነው።

በሁለቱ አገራት መካከል በንግድ፣ በጸጥታና አቅም ግንባታ ዘርፍ በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ መደረሱንም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ በመገንባቱ ሂደት የሁሉም ትብብር ሊጠናከር ይገባል!

አሸባሪው ትህነግ አገር ለማፍረስ የያዘውን ግብ ለማሳካት ባለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በአማራና አፋር ክልሎች በፈጸመው ወረራና በከፈተው ጦርነት ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት ማድረሱ ይታወሳል። አሸባሪው ቡድን በርካታ መሠረተ ልማቶችን ዘርፏል፤ አውድሟል። ውድመት ከደረሰባቸው መካከል የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ እና የኃይል መሠረተ ልማቶች እንዲሁም መንግሥታዊ ተቋማት እና የግል ባለሀብቶች ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሽ ናቸው።

በዚህም አሸባሪው ትህነግ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ዙር በወረረውና በከፈተው ጦርነት የወደሙት በርካታ መሠረተ ልማቶች ናቸው። ለአብነት እንኳን በአማራና አፋር ክልሎች 42 ሆስፒታሎች፣ 523 ጤና ጣቢያዎች፣ 2 ሺህ 359 ጤና ኬላዎች ዘረፋና ውድመት ተፈፅሞባቸዋል።

በመሠረተ ልማቶቹ ላይ በደረሰው ውድመት ምክንያትም በአካባቢው ለማህበረሰቡ ይሰጥ የነበረው የጤና አገልግሎት ተስተጓጉሎ ቆይቷል። በአካባቢዎቹ የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ከመሠረታዊ እስከ ከፍተኛ የጤና አገልግሎቶች እንዳያገኙ እንቅፋት ፈጥሯል። ነፍሰጡር እናቶች፣ ሕፃናትና አረጋውያን በአቅራቢያቸው የጤና ተቋማትን አገልግሎት ባለማግኘታቸው ከህመም ስቃይ ጀምሮ እስከ ሞት አስተናግደዋል። በዚህም ከፍተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አጋጥሟል። ይህንኑ በአማራ እና አፋር ክልሎች በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ የጤና ተቋማትን መልሶ ለመገንባት ከ36 ቢሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ወጪን የሚጠይቅ ሆኗል።

ሁለት ዓመታት ባስቆጠረው የሰሜኑ ጦርነት ከጤና ተቋማት ባሻገር የትምህርት ተቋማትም ውድመትና ዘረፋ ተፈፅሞባቸዋል። ሕፃናትና ታዳጊዎች ከትምህርት ሥርዓቱ ውጪ ሆነዋል፤ ከየአካባቢያቸው ተፈናቅለው ስደተኛ እስከመሆን ደርሰዋል። ዛሬም ድረስ ወደ ትምህርት ሥርዓቱ ያልገቡ ብዙዎች ናቸው።

በአማራ ክልል በትምህርት ተቋማት ላይ ብቻ የደረሰው ጠቅላላ የጉዳት መጠን ከ5 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሲሆን፣ በአፋርም በተመሳሳይ በትምህርት ተቋማት ላይ ዝርፊያና ውድመት ደርሷል። እንዲሁም የንጹህ መጠጥ ውሃ እና የኃይል መሠረተ ልማቶችም በትህነግ የወደሙ መሠረተ ልማቶች ናቸው። ይህም አገርን ለከፍተኛ ኪሳራ ዜጎችን ለሰብአዊ ጉዳት ዳርጓል።

አሸባሪው ትህነግ በመሠረተ ልማቶች ላይ ከፍተኛ ውድመት ቢፈጽምም በማህበረሰቡ፣ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በዲያስፖራው ያላሰለሰ ትጋት እና ትብብር በተወሰነ ደረጃ አንዳንድ የፈራረሱና የተዘረፉ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ የመገንባትና የመጠገን እንዲሁም ተፈናቃዮችን የመደገፍና የማቋቋም ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተወሰኑ የጤና ተቋማትና ትምህርት ቤቶች ወደ ተግባራቸው ገብተዋል። ሆኖም ግን የወደሙትና የተዘረፉት መሠረተ ልማቶች ካላቸው ብዛት እና ከሚጠይቁት ሀብት መጠን ሙሉ ለሙሉ ተጠግነው አገልግሎት እየሰጡ አይደሉም። ከወደሙ የመሠረተ ልማቶች ብዛት እና ከሚጠይቀው ወጪ አንጻር አሁንም ሰፊ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል፤ አሁንም ከፍተኛ ሀብት ይፈልጋል።

ስለዚህ ኅብረተሰቡ የጤና አገልግሎት፣ ትምህርት እንዲሁም ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኝባቸውን መሠረተ ልማቶች ትኩረት ሰጥቶ መልሶ መገንባት ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር አለመሆኑን ተገንዝቦ ትብብርና እርዳታውን ሊቀጥል ይገባል። የወደሙና የተዘረፉ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባት በሚደረገው ሂደት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያሉ ዜጎች፣ ተቋማት፣ ተባባሪ አካላት ሁሉ ድጋፍ ሊያደርጉ ያስፈልጋል።

አሸባሪው ትህነግ ባለው አገር የማፍረስ ራዕይ ያወደማቸው መሠረተ ልማቶችን መልሶ የመገንባቱ ሥራ በመንግሥት አቅም ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ አሁንም ሁሉም አካላት ትብብሩን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በውስጥ በውጭም ያሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለአገርና ለሕዝብ ያለንን አጋርነት የምናሳየው ለአገር ደራሹ የአገር ልጅ መሆኑን በማሳየትና ይሄንኑ በተግባር በማስመስከር ጭምር ነው። 50 ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰዎች ጌጥ መሆኑን የምናየው ይሄንን በአገር ላይ የወደቀን አደጋና ሸክም እያንዳንዳችን ስንሸከም መሆኑ ግልጽ ነው።

በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት በተለያዩ ግጭቶችና በተፈጥሮ አደጋዎች ለተፈናቀሉና ለተጎዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰብአዊ ዕርዳታ ድጋፍ ማድረግና በጦርነቱ እና በግጭት ምክንያት የወደሙና የፈረሱ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ተቋማትን መልሶ በመገንባት ሂደቱ ዋና ተዋናይ ልንሆን ይገባል። እስካሁን በመልሶ መገንባቱ ድጋፍና ትብብር ያደረጉትን እያመሰገንን በቀጣይም የነበረውን መተባበር አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዐምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአዲሱ መንግሥት የአንድ ዓመት ጉዞ እና ቀጣይ የቤት ሥራዎች

**በምስጋና ፍቅሩ**

በስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ተወዳድሮ እና አሸንፎ ሀገሪቱንም እየመራ ያለው አዲሱ መንግሥት ምሥረታውን ያካሄደው በወርሃ መስከረም ነበር ። አንድ ዓመትን ያስቆጠረው አዲሱ መንግሥትም በአጭር ጊዜ እና ረዘም ባሉ ዓመታት ውስጥ የሚያከውናቸውን በርካታ ሥራዎች ለመሥራት ከማቀድ በተጨማሪ እቅዶቹን የተሳካ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆነ ይታወቃል ። እኔም በዛሬው መጣጥፌ ከለውጡ ማግስት በምርጫ ስልጣን የያዘው መንግስት በአንድ ዓመት ጉዞው የነበሩትን ጥንካሬዎች እንዲሁም የነበሩበትን ደካማ ጎኖች በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ።

መንግሥት በተለይም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን አጠናቅቆ ከማስመረቅ አንጻር እጅግ የሚያስመሰግነውን ስራ የሠራ ሲሆን፤ በዚህ ረገድ ፕሮጀክቶች ቀድሞ የነበረባቸውን በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት ተጠናቅቀው ለሚፈለግባቸው አገልግሎት ያለመዋልን ችግር ያስቀረ ዘርፈ ብዙ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ አጠናቅቆ ህብረተሰቡን እንዲጠቀሙ ማድረጉ ይበል እና ይቀጥል የሚያሰኝ ነገር ነው ። እዚህ ጋ ሳይጠቀስ የማያልፈው የዓባይ ግድብም ቢሆን ለሦስተኛ ዙር ውሃ መሞላት መቻሉም መንግሥት ይህንን ፕሮጀክት እውን እንዲሆን ማስቀጠልና ለውጤት እንዲበቃ የማድረጉም ነገር በቀላሉና ሁለተኛው ተርባይን ወደ ኃይል ማመንጨት ስራ መግባቱ በትልቁ የሚነገር ስኬት ነው ።

በሌሎች አገራት ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየሆነ የመጣው ተገጣጣሚ ቤቶችን በመገንባት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ማድረጉም የዜጎችን ችግር ከመፍታት አኳያ ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ በመሆኑ በዚህ ይቀጥል የሚያስብል ሥራ ነው ። ይሁን እንጂ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በተመለከተ መንግሥት እንደ መንግሥት ሥራውን ከተረከበ በኋላ ይህ ነው ተብሎ የሚነገር ለዐይን የሚሞላ ሥራ አልታየም ቢባል ብዙዎቻችንን ሊያስማማ የሚችል ነው ። እንደውም በሰኔ ወር 2014 ዓ.ም የወጣው የጋራ መኖሪያ ቤት እጣ ጉዳይ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በድጋሚ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ይወጣል ተብሎ በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት ቢገለጽም እስካሁን እጣው በድጋሚ ለምን እንዳልወጣ የተገለጸ ነገር የለም ። ይህም የሕዝብን አመኔታ የሚያሳጣ ድርጊት በመሆኑ መንግሥት አንድ መፍትሄ ሊያበጅለት ይገባል ።

በተጨማሪም መንግሥት የቤት ተከራዮች ላይ ኪራይ እንዳይጨምር ለማድረግ በተለያዩ ጊዜ አከራዮች ዋጋ እንዳይጨምሩ እና ተከራዮችን እንዳያስወጡ ማድረጉ በአንድ በኩል የሚመሠገን ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለቤት ኪራይ መናር የአከራዮች ብቻ ሚና ሳይሆን ለዚህ ችግር መበራከት እንዲሁም በመባባሱ በኩል ድርሻውን እየተወጣ ያለውን ህገ ወጥ ደላላ ለመቆጣጠር አስተማሪ የሆነ ሥራ የተሠራ አይመስልም ። ይህ ችግር ደግሞ የህዝቡን ብሶትና ችግር የሚያባባስ ድርጊት መሆኑን ተገንዝቦ መንግሥት በቀጣይ ሊቀርፈው የሚገባው ነው ።

መንግሥት ከመሥረታው በኋላ ከሠራቸው ሥራዎች በገበያ በኩል የኑሮ ውደነቱን ለመቀነስ በርካታ ጥረቶች አድርጓል፤ በተወሰነ መልኩም ችግሩን መከላከል ችሏል ። ሆኖም ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የበለጠ መሥራት ይጠበቅበታል ። በተለይ ከህገ ወጥ ንግድ ጋር በተያያዘ አንድ ምርት ዋጋ ከመጠን በላይ ሲወደድ ይህንን ተከታትሎ ጥፋተኞች ላይ ርምጃ ወስዶ ለሌሎች መማሪያ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ሳይንስና ቴክኖሎጂውን ከማስፋት አንጻርም በዓይነቱ ልዩ የሆነ የሳይንስ ሙዚየም እውን ማድረግ ተችሏል፤ በቴሌኮም ዘርፉም ተወዳዳሪነትን ለማስፋት የ ሳፋሪ ኮም ያሉ የቴሌኮም ኩባንያዎች በሀገር ወስጥ ሥራቸውን እንዲጀምሩ ሆኗል ። በዚህም ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥርላቸው ሲሆን ለሕብረተሰቡም ቢሆን አማራጭ መቅረቡ የሚያስመሰግነው ሥራ ነው ። በቀጣይም የባንክና ሌሎች ዘርፎች ላይ መሰል ማሻሻያዎችን መመልከት ተገቢ ይሆናል ። ይሄም የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር ሀገሪቱንም በኢኮኖሚ እንድታድግ እና በባንኩ ዘርፍም ጥሩ ውድድር እንዲኖር ያስችላል ።

ከሰላምና ደህንነት አንጻርም መንግስት በሆደ ሰፊነት ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ የአገርን ክብርና ጥቅም ባስከበረ መልኩ የሚሄድባቸው መንገዶች ይበል የሚያሰኙ ናቸው ። በዚህ ረገድ ምንም እንኳን ለስኬት አይብቃ እንጂ ከአሸባሪው ትህነግ ጋር ያለውን ልዩነት በድርድር ለመፍታት የሄደበት ርቀት የሚያስመሰግን ነው ። ዛሬም ቢሆን ከጦርነት የሚገኝ ትርፍ እንደሌለ እና የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች በጦርነቱ ምክንያት ሕይወታቸውን መገበር፤ የአገርም አንጡራ ሃብት መውደም ስለሌለበት መንግስት ለሰላም የሰጠው እድል የአገርን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ሊቀጥል የሚገባው ነው ። ምክንያቱም በኑሮ ወድነት እና በመሰል ችግሮች እየተናጠች ላለች ሀገር ጦርነቱ የኢኮኖሚ ድቀት ከማከናነብ ውጭ ይዞላት የሚመጣ ትርፍ ባለመኖሩ መንግሥት ከዚህ በፊት ሲያደርጋቸው የነበሩትን የሠላም ጅምሮች የበለጠ መሥራት ይጠበቅበታል ። ለሠላም የተዘረጉ እጆችም መታጠፍ የለባቸውም ።

በዚህ ረገድ ብዙዎች መንግሥት ሠላምን በማስፈን እና እዚህም እዛም የሚታየውን ግጭት ለመፍታት አቅም እንደሚኖረው ያምናሉ ። ይሁን እንጂ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ሠዎች በማንነታቸው ምክንያት ሕይወታቸው እየጠቀጠፈ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመንግስትን ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡም አልታጡም ። በመሆኑም ይህንን ያላባራ ችግር መንግሥት ሊያስወግደውና የዜጎች በሠላም ወጥቶ መግባት እና የመሥራት መብታቸው ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሠራት ይጠበቅበታል ።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ከምርጫው ማግስት መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ ከዚህ ቀደም በሀገራችን ብዙም ያልተስተዋለውን ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ስልጣን የማጋራቱ ነው ። ይህም እንደ መንግሥት ተባብሮ እና ተደጋግፎ ከመሥራት በተጨማሪ ብዙ ጊዜ ‹ትችት እንጂ ሥራ አይችሉም› ተብለው ለሚነቀፉት ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለሀገራቸው የአቅማቸውን እንዲያደርጉ እድል መስጠቱም የሚያስመሰግነው ሥራ ሲሆን፤ ይህ አይነቱ ድርጊት ለሌሎች ሀገራት ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው ብሎ ደፍሮ መናገርም ይቻላል ። ከዚህ ጋር በተያያዘም እንደ መንግሥት በጣም ጥሩ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ከሚታዩት ሥራዎች መካከል በተለይም የትህምርት ዘርፉ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

ለአብነት እናንሳ ከተባለም የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ በኩል በያዝነው ዓመት ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመውጫ ፈተና ሀገሪቱ ብቁ እና ተወዳዳሪ ዜጎችን እንድታፈራ የሚያስችል በመሆኑ በመንግስት በኩል ይህ ዓይነቱ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ መሆኑን ለመረዳት አመታትን መጠበቅ አያሻም ። የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱም ቢሆን ሌላው በበጎ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ነው ። ፈተናው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መሰጠቱ እና ለመኮራረጅ እንዳያመች አራት የነበሩት የፈተና ኮዶች ወደ 12 ከፍ እንዲል መደረጉም የነገው ሀገር ተረካቢ ዜጋ በራሱ ጥረት የሚሠራ፣ ብቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችለው ነው ።

በግብርናው፣ ኢንዱስትሪ፣ ማዕድን፣... ዘርፎች የተሰጠው ትኩረት፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የከተማ ግብርና እንዲለመድ ለአትክልት ልማት የሠጠውን ጉዳይ ማንሳቱ ተገቢ ነው ። ከታች ከወረዳ ጀምሮ እስከ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ድረስ ለአብነት እየተተከሉ ያሉ እና በቀላሉ ለምግብነት የሚደርሱ ተክሎችን እንዲተከሉ ማስቻል እና ማስተማር መንግሥትን የሚያስመሰግነው ሥራ ነው ። እኔም እነዚህን መሰል በመልካምም በችግርም የሚነሱ ነገሮችን መጠቃቀሴ መንግስት ከጥንካሬው ብርታትን፣ ከድክመቱ ቁጭትን ይዞ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ስራ እንዲያከናውን በማሰብ ነው ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ፈተና ያልበገረው ዙሪያ መለስ የመሪነት ሚና ...!?

የአሜሪካ 26ኛው ፕሬዚዳንት ቴዎዶር ሩዝቬልት በአንድ ወቅት "ጦርነት ባይኖር፣ የጦር ገበሬ የሆነ ጄነራል አይኖርህም። ያለ ከባድ ቀውስና ፈተና ታላቅ መሪ ልታፈራ አትችልም። አብርሀም ሊንከን የጦርነት ጊዜ ፕሬዚዳንት ባይሆን ኖሮ ዛሬ ላታስታውሰው ትችላለህ።" ብለው ነበር። እነዚህ አራት ዓመታት እንደ ሀገር፣ ሕዝብና ተቋማት በብርቱ የተፈተንባቸው ቢሆንም የዚች ሀገር መሪ ላይ ግን ፈተናው ከወፍጮ ድንጋይ ጋር ታስሮ ወደ ጥልቁ ጋር ከመውረድ የከበደ ነው። የሀገር፣ የሕዝብና ተቋማት ፈተና ቀድሞ መሪ ላይ የሚወድቅ ነውና። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ አመራርነት ከመጡበት ጊዜ አንስቶ እንደ መርግ በከበዱ ኅልቆ መሳፍርት በሌላቸው ፈተናዎች አልፈዋል። እያለፉም ይገኛል። እነዚህ ፈተናዎች ይዘውት የመጡ ግንባረ ብዙ ጦርነት፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፤ የኦነግ ሸኔና የቢጤዎቹ የንጹሐን ጭፍጨፋ፣ በዩኒቨርሲቲዎች የሚያባራ የማይመስል በጎሳ ላይ የተመሠረተ ግጭት፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀዬአቸው የተፈናቀሉበት፤ በኦሮሚያና በሶማሊያ ክልሎች የተከሰተ ድርቅ፤ የዋጋ ግሽበቱን ተከትሎ የተፈጠረ የኑሮ ውድነት፤ የተጠና የኢኮኖሚ አሻጥር፤ የዓለማቀፍ ሚዲያው፣ የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋማትና ዓለማቀፉ ማኅበረሰብ ተቀናጅተውና ግንባር ፈጥረው በሀገራችን ላይ ያሳረፉት ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖ፤ ወዘተረፈ. ደቅነውት የነበርና የአለ አደጋ ሁላችንንም የፈተኑን ቢሆንም ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት መሪ ላይ ሲሆን ግን የከፋ ነው።

ወርቅ በከዉር እንደሚፈተነው የሀገር መሪም እንዲህ በሀገራዊ አሳርና ፈተና አብሮ ይፈተናል ። አንድን መሪ መሪ የሚያደርገውም እነዚህን ፈተናዎች በጽናትና በአሸናፊነት መሻገር ሲችል ነው ። ታዋቂዋ የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ታሪክ አጥኝና ደራሲ ዶሪስ ከረንስ ጉድዊን፤ "LEADERSHIP" በተሰኘ ግሩም ድንቅ መጽሐፏ፣ "የመሪዎችን አፈጣጠርና አነሳስ በቅርብ የሚያጠኑ የዘርፉ ልሒቃን የተዋጣለት መሪ ማለት በመከረና በፈተና ሳይበገር በጽናት ለዓላማው ስኬት ሌት ተቀን የታመነ ነው ትላለች። "የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን የአመራር ብቃትም ሆነ ድክመት ልሒቃን በጥናትና በምርምር መዝነው ወደፊት የሚያሳውቁን ቢሆንም፤ ታሪክና ትውልድም በተራው የራሱን ፍርድ ቢሰጥም፤ አይደለም እንዲህ ባለ ፈተና ተረጋግቶና ጸንቶ ኢትዮጵያን ያህል ታላቅ ሀገር መምራት ይቅርና አርሴናል የተሸነፈ ዕለት እንቅልፍ አጥቼ የማድርና ሰው በአጠገቤ ባለፈ ቁጥር ነገር ነገር ይለኝ የነበር ሰው የጠቅላይ ሚኒስትሩን በቀውስ መሀከል ሆኖ የተገለጠ የአመራር ጥበብ ባላደንቅና እውቅና ባልሰጥ ንፍገት ስለሚሆንብኝ ፤ ሰሞነኛውን ዘመኑንና ትውልዱን የዋጀ የሳይንስ ሙዚየም ምረቃ መነሻ አድርጌ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ BIBLICAL/ሊባል በሚችል መከራና ፈተና መካከል ሆነው ፣ ሳይበገሩና አንድም ቀን ሸብረክ ሳይሉና ጥርሳቸውን ነክሰው እየቃተቱ አይናቸውን ከአፋቸው ከማትጠፋ ኢትዮጵያ ለቅጽበት ሳያነሱ ያከናወኗቸውንና ለሀገር ወሳኝ መታጠፊያ የሆኖ ግዙፍ ግዙፍ ፕሮጀክቶችንና ተግባራትን ከማነሳሳቴ በፊት ፤ እኔን ጨምሮ አይደለም ታሪክን በእነዚህ አራት ዓመታት እንኳ ያለፍንባቸውን መከራዎችና አሳሮች የምንረሳ ዝንጉና ባተሌ ስለሆን በወፍ በረር መለስ ብለን አብረን እንቆዝም ።

በተደጋጋሚ እንደምለው በዚች ሀገር የ"100"፣ የ3ሺህም ሆነ የ7 ሺህ ዓመት ዘመናዊ ሆነ ጥንታዊ የሀገረ መንግሥት ታሪክ እንደ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መንግሥት እና እንደዚህ ትውልድና ሕዝብ በኃይለኛ የውቅያኖስ ማዕበል (ሱናሚ ) መካከል እንደምትቀዝፍ ታንኳ ከየአቅጣጫው የተላጋ ፣ የተናወጠ ፣ የተፈተነና መልሕቁን ለመጣል የተቸገረ የለም ማለት እችላለሁ ። ታሪካዊ ንጽጽሬ ላይ የዘመነ ጓዴነት/contemporaries/ ጥያቄ የሚያነሳ ካለ ደግሞ እንዲህ ላስተካክለው:- ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ በየትኛው አህጉር ያለ ሀገርና ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ የተፈተነ የለም። የመንም ፣ ሊቢያም ፣ ሶሪያምና ሶማሊያም ፣ ሌላም ሀገር ቢሆን ። በሰሜን ዕዝ ላይ ትውልድም ሆነ ታሪክ ይቅር የማይለው ክህደትና ጭፍጨፋ የተፈጸመበት ፤ በአማራና በአፋር ክልሎች በአሸባሪው ሕወሓት ከአንድም ሁለት ሶስት ጊዜ ጦርነት በከፈተበት ፤ በዚህ የተነሳ ከ12 ሚሊዮን በላይ ወገኖች ተፈናቃይና ተረጂ በሆኑበት ፤ በታላቁ የሕዳሴ ግድብ የተነሳ ግብጽና ግብረ አበሮቿ እንደ ውጋት ቀስፈው በያዙን ወቅት ፤ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ የአርብቶ አደሩ የሕልውና ዋስትና የሆኑ እንስሳት አልቀው በሚሊዮኖች የሚገመት ሕዝብ የዕለት ደራሽ እርዳታ ፈላጊ በሆነበት ፤ በአናቱ የቀደሙትንና ሰሞነኛዎችን ሳይጨምር እስከ አለፈው ዓመት በአገሪቱ 120 ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ጭፍጨፋዎች ፣ ጥቃቶችና ግጭቶች በተቀናጀ አግባብ መፈጸማቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ መናገራቸውን ያስታውሷል ። የሕወሓት ቡችሎች ተናበውና ተቀናጅተው በሀገሪቱ አራቱም አቅጣጫዎች ጭፍጨፋና ጥቃት በከፈቱበት ፤ በመላ አገሪቱ እየተስተዋለ ያለው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ሕዝቡን ክፉኛ እያማረረ ባለበት በዚህ ፈታኝ ሰዓት ፤ ስነ ምግባር የጎደላቸው ስግብግብ ነጋዴዎችና ደላላዎች ፤ ብልሹ ከሆነው የግብይት ሥርዓት ጋር አብረው ግሽበቱንና የኑሮ ውድነቱን እያባባሱ ባሉበት ቀውጢ ሰዓት ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተስፋ እንድንሰንቅ ፤ የብሩህ ተስፋ እሸት እንድንቀምስ አድርገዋል ። ገና ብዙ ያልተሻገርናቸው ፈተናዎች ቢኖሩም ።

ይሁንና ሁሉም ነገር ተስፋ አስቆራጭና ድቅድቅ ጨለማ ነው ማለት አይደለም ። ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ከክሽፈት ተርፎ በሁለት ተርባይን 550 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት መቻሉ በራሱ ትልቅ የአመራራቸው ስኬት ቢሆንም የቀጣናውን ጂኦፖለቲካ በመበወዝ የሚኖረው ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነው ። በድህነታችንና በተመጽዋችነታችን ሳቢያ ፖለቲካዊ ብቻ የነበረውን ግማሽ የነጻነትና የሉዓላዊነት ታሪካችን ሙሉ የሚያደርግ የስንዴ ልማትና አጠቃላይ የግብርና ውልጠት /transformation/ሌላው ተስፋ የሚያሰንቅ ተግባር ነው ። ሀገራችን በ2014 ዓም መኸርን ሳይጨምር በበጋ መስኖ ልማት ብቻ 25 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት የተቻለ ሲሆን ፤ በመኸር ደግሞ ወደ 60 ሚሊዮን የሚጠጋ ኩንታል ስንዴ ፤ በዘንድሮው ዓመትም 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እቅድ መያዙ ሌላው የአርቆ ተመልካችና የበሰለ አመራር አብነት ከመሆኑ ባሻገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ወሳኝ መታጠፊያ ነው ። ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያ በቀጣዩ ዓመት ከግብጽ ቀጥላ ስንዴን ለዓለማቀፍ ገበያ የምታቀርብ 2ኛዋ ሀገር እንደምትሆን እየተገለጸ ይገኛል። ኩታ ገጠም ግብርና እና ሜካናይዜሽን ላይ እየተሠራ ያለው ሥራም ተስፋን የሚያለመልም ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም ሉዓላዊነታችንን ሙሉ በኩልዬ የሚያደርግ ነው ። የአረንጓዴ አሻራውና የአትክልትና ፍራፍሬ ልማቱም የብሩህ ተስፋችን ሌላው ቡቃያ ነው ። በአረንጓዴ አሻራ ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል መቻሉ ሌላው እጅን ባፍ ያስጫነ ስኬት ነው ። የአብርኆት ግዙፍ ቤተ መጽሐፍት ፤ ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክቶች ፤ የእነ ኮይሻ ፣ ጎርጎራ ፣ወንጪ ፕሮጀክቶችም አይን ገላጭና መስፈንጠሪያ ሆነው ከሚያገለግሉን ሜጋ ፕሮጀክቶች ተርታ የሚሰለፉ ናቸው ። እኛም ከሰናይ ተግባራት ይልቅ በእኩያኑ፣ በሴራ ፣ በጎሰኝነትና በሐሰተኛ መረጃ ተወስደን ፤ ዓለማቀፉ ማኅበረሰቡና ሚዲያም ከእውነት ጋር ከመቆም ይልቅ ከሕወሓት ጎን መቆም ስለፈለገ እንጂ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀሳብ አፍላቂነትና አመራር የተመዘገቡ አንጸባራቂ ውጤቶች በታሪክ ታይተው የማያውቁ ከመሆናቸው ባሻገር የሀገሪቱን መጻኢ እድል በምቹ መደላድል የሚያስቀምጡ መሆናቸውን ደረትን ነፍቶ በኩራት መመስከር የሚያስችሉ ናቸው ።

ሀገራዊ ምክክር ለማድረግ መንግሥት ኮሚሽን በአዋጅ ማቋቋሙና ኮሚሽኖች በገለልተኛ አካል እንዲሰየሙ መደረጉ ፤ በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል ነው ። በማንነት በልዩነትና በጥላቻ የተጎነቆለውን ፖለቲካችንን እልባት የሚሰጥ ነው ። ሀገረ መንግሥቱን ከተቀለሰበት ድቡሽት አንስቶ በጽኑ መሠረት ላይ የሚያንጽ ነው ። ትውልዶች ለዘመናት ሲያነሷቸው ሲታገሉላቸውና መስዋዕት ሲከፍሉላቸው የኖሩ ጥያቄዎችን በማያዳግም ሁኔታ የሚመልስ ነው ። ሀገራዊ ምክክሩ የጋራ አገር ፣ የጋራ ሕልም ፣ የጋራ ራዕይ ፣ የጋራ ሰንደቅ አላማ ፣ የጋራ ጀግና ፣ የጋራ ታሪክ ፣ ወዘተረፈ. እንዲኖረን የሚያግዝ ነው ። ገለልተኛነቱ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ከተመለሱና በቅንና ንጹሕ ሕሊና ከተመራ የትውልድ ተስፋና ለአገርም ወሳኝ መታጠፊያ/critical juncture/ ነው ። ሀገርን እንደ ንስር የሚያድስና በከፍታ የሚያበር ነው ። ከእነ ውስንነቶቹ በስኬት የተጠናቀቀው ሀገር አቀፍ ምርጫም በልኩ እውቅና ሊቸረው ይገባል ። በተለይ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ማለትም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ፣ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን ኮሚሽንናና የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምንና ፍርድ ቤቶችንና የፍትሕ አካላትን በነጻነትና በገለልተኝነት ለማቋቋም የተሄደበት እርቀት ይበል የሚያሰኝ ነው ። በተለይ የሀገራችን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የመጨረሻ ምሽግ በሆነው የመከላከያ ሠራዊት ፣ በሌሎች የጸጥታና የደህንነት ተቋማት ላይ የመጣው ተጨባጭ ለውጥም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ዙሪያ መለስ ዕይታና የአመራር ሚና የሚያሳይ ነው ። አንዱን ይዞ ሌላውን በመጣል ችግሮቻችንን መፍታት እንደማንችል በተግባር አመልክተውናል ።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና ዘመናዊ የሳይንስ ሙዚየም ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል ። ግዙፍና በቀለበት ቅርፀ የተገነባው ሕንፃ ከ15 ሺህ ሜትር ካሬ በሚበልጥ መሬት ላይ የተንጣለለ ሲሆን ፤ 132 ሜትርም ይረዝማል ። ሙዚየሙ አዳዲስ ተሞክሮዎችና ዕውቀቶች የሚቀሰሙበት መድረክም መሆኑ ፤ ዛሬንና ነገን በአንድ ላይ አያይዞ ሳይንስን ጥበባዊ በሆነ መንገድ የያዘ ፤ ግቢውም ሰባት ሺህ ሄክታር እንደሚሰፋ ተገልጿል ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም በቲዊተራቸው ፤ "የኢትዮጵያ ሳይንስ ሙዚየምን መርቀን ከፍተናል። የቴክኖሎጂ ዐውደ ርዕይ አስጀምረናል። የመጀመሪያውን የፓን አፍሪካን አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኮንፈረንስ ከፍተናል። ምክንያቱም አፍሪካን ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በማብቃት በአህጉሪቱ መተሣሰርን፣ መማማርንና በጋራ መፍጠርን ለማምጣት ሁሉም አስፈላጊ በመሆናቸው ነው"ብለዋል ። ቀደም ሲል የብሔራዊ ደህንነትና የመረጃ አገልግሎትንና የሰው ሰራሽ ክህሎት/ አርቴፊሻል ኢንተሌጀንስ/ተቋማትን በመመሥረት ረገድ እርሾ ሆነዋል። ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ፤ ሀገራችን የመጀመሪያዋን ሳተላይት ወደ ሕዋ ያስወነጨፈችውም በእሳቸው አመራር ነው ። ለዚህ ራዕይ እውን መሆን ከጥንስሱ ጀምሮ የእሳቸው ተሳትፎ የጎላ ነው ።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም የስፔስ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የቀድሞ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሰለሞን በላይና ባልደረቦቹ ራዕይ እና የሌት ተቀን ጥረት ውጤት ማብሰሪያ እና የህዳሴ ምልክት የሆነችው የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ሳተላይት ETRSS – 1 / Ethiopian Remote Sensing Satellite / ቻይና ከሚገኘው የስፔስ ሳይንስ አካዳሚ የሳተላይት ማስወንጨፊያ ማዕከል ለኢትዮጵያ መረጃ ልታቀብል ሰንደቃችንን አንግባ የቀደሚትን ዘጠኝ የአፍሪካ ሀገራትን ጨምሮ ወደ 9ሺህ የሚጠጉ ሳተላይቶች በመቀላቀል ኢትዮጵያ 41ኛ ሆና የባለሳተላይት ሀገራትን ዝርዝር ተቀላቅላለች። "...ከ8 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጭ የተደረገባት ሳተላይቷ ከመጠቀች በኋላ በ30 ደቂቃ የተያዘላትን የ700 ኪሎ ሜትር ከፍታ orbital slot ትይዛለች። ከዚያ በኋላ ፍተሻውና የማስተላለፉ ሂደት በ1ወር ከ7 ቀን ይጠናቀቃል። ከዚያ ቀጥሎ በሚኖረው አንድ ወር የምታስተላልፈው መረጃ ትክክል መሆን አለመሆኑ ከተመረመረና የምትገኝበት ሁኔታም ከተረጋገጠ በኋላ ርክክቡ ይፈፀማል። ከዚያ ሳተላይቷ እስከ 10 ዓመት ድረስ አገልግሎት ትሰጣለች ። ኢትዮጵያ እነዚህን መሰል የሳተላይት መረጃዎች እስካሁን የምታገኘው ይህን አገልግሎት ከሚሰጡ የውጭ ሀገር ድርጅቶች በግዢ ነው። ሀገሪቱ ለሳተላይት ምስሎች ግዢ ብቻ ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ በየዓመቱ ታወጣለች። ሀገሪቱ ለሳተላይት መረጃ የምታወጣው ወጪ ከዚህም የላቀ ነበር ብለው ነበር ዶ/ር ሰለሞን ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ከ2008 ዓ.ም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ሳሉ ጀምሮ ለስፔስ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ልዩ ድጋፍና ክትትል ያደርጉ እንደነበርና ተቋሙ የራሱ ሳተላይት ለማምጠቅ የበቃውም በእርሳቸው ጥረት መሆኑን ዶ/ር ሰለሞን አስታውቀው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ 2ኛውን ሳተላይት ለማምጠቅ ከሁለት ዓመት በላይ የፈጀውን የአዋጭነት ጥናቱን አጠናቃ ሀብት የማፈላለግ ሥራውን በማከናወን ላይ መሆኗን የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የቀድሞው አይረሳም ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሰለሞን በላይ ይፋ አድርገዋል። በቀጣይ የሚመጥቀው የኮሙዩኒኬሽን ሳተላይት ሲሆን ፤ ሳተላይቱ 60 ኩንታል የሚመዝን ሲሆን ከምድራችን 36ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በህዋ ይቀመጣል። ለሳተላይቱ ግንባታና ለማስወንጨፍ የሚያስፈልገውን ወደ 400 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ በረጅም ጊዜ ብድርና በአነስተኛ ወለድ ለማግኘት መንግሥት በቅንጅትና በቁርጠኝነት በመሥራት ላይ መሆኑን እና በቀጣዩ የበጀት ዓመት ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቆ ፕሮጀክቱ ይፋ ይደረጋል።

ሀገራችን በሚቀጥሉት 15 ዓመታት የሳተላይቶቿን ቁጥር 11 ለማድረስ አበክራ በመሥራት ላይ መሆኗን ከዋና ዳይሬክተሩ አንደበት ከመስማት በላይ ለዚህ ትውልድ ልብን በሀሴት የሚሞላ ምን ብስራት አለ!? ይሁንና ሀገራችን ከ3ና 4ሺህ ዓመታት በፊት በህዋ ምርምር ዘርፍ የዛሬዎቹን ልዕለ ኃያላን ከፊት ሆና ስትመራ እንደነበር የጥንት ብራና መጽሐፍትና ስንክ ሳሮች ዋቢ ከመሆናቸው ባሻገር ዓለማቀፉ የአስትሮኖሚ ኅብረት በሀገራችን ልዕልት፣ ንግሥትና ንጉሥ ስም ኅብረ ከዋክብት constellations መሰየሙን ስንቶቻችን ይሆን የምናውቀው!? ስለ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የስነ– ፈለክ /የሕዋ/ እውቀትና በዘመን አቆጣጠር ምን ያህል የተራቀቁ እንደነበሩ በማስረጃ የሚተነትነው የሮዳስ ታደሰና ጌትነት ፈለቀ (ሁሉም ፒ ኤች ዲ ሠርተዋል)። በጋራ በደረሱት፤ " አንድሮሜዳ " መጽሐፍ ላይ ፤"... ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ያሉ የውጭው ዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ...' ጥንታዊ ዘር' በመባል የምትታወቀውን ኢትዮጵያን ... አውሮፓና እስያ ባልሰለጠኑበት ዘመን ...ፍልስፍና፣ ሥነ ጽሑፍ ፣ ሒሳብ ፣ ግብርና ፣ ሕክምና ፣የከዋክብት ጥናት ...የኢትዮጵያውያን ነባር ሀገር በቀል እውቀቶች እንደነበሩ ተናግረዋል።... " ይህ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለስነ ፈለክ የማይናወጥ መሠረት እንደነበራቸው ያረጋግጣል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ ባለቤት መሆኗን እና ለስነ– ፈለክ ምርምር ወረት፣ መነሻ እንደነበራት የሚያረጋግጡ የቀደምት ሊቃውንት እማኝነት ከፍ ሲል በተገለፀው መፅሐፍ እንደሚከተለው ተዘግቧል። "60 ዓመት ቅድመ ልደት ክርስቶስ የነበረው ዲዎዶርስ ሴኩለስ የተባለ የታሪክ ሊቅ ' አውሮፓውያን ኋላ ቀር እድገት አኗኗር ላይ በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ታላቅ ስልጣኔ ላይ የነበረች ... ኢትዮጵያውያን ለግብጻውያን ስልጣኔ ያስጀመሩና እስከ ሕንድ ድረስ የገዙ ናቸው። ' ... በ700 ዓ.ም የነበረው የቤዛንታይኑ እስቲፋንስ ባካሄደው ጥልቅ ጥናት ' ኢትዮጵያ መሬታችን ላይ የተመሠረተች የመጀመሪያ ሀገር ናት ' ሲል አርኖልድ ኸርማን ሉድዊግ የተባለ የጀርመናዊ የታሪክ ፀሐፊ ደግሞ ' ኢትዮጵያን የመሰለ ጥንታዊ ሀገር ወዴት ይገኛል!?' ሲል ይሞግታል ... ከ800 ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት የኖረው ሆሜር ኢሊያድና እና ኦዲሴይ በተባሉ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎቹ ኢትዮጵያውያን ' እስከ መሬት ጫፍ ድረስ የሚኖሩና ከአምላክ ጋር ቅርበት ያላቸው ' በማለት ይገልጻቸዋል።

የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ሔሮዶቶስ ኢትዮጵያውያንን 'ከሰሐራ በታች የሚኖሩ፣ ጥቁር ቆዳ ያላቸው ...ብልሆች፣ በዓላቶቻቸውና ሀሴታቸውም ሳይቀር አማልክትን ስለሚያስደስት የአማልክት አምላክ እየሄደ በዓላቱን በደስታ አብሯቸው ያሳልፋል ' ብሏል። ...ዲዮዶር የተባለ የሮም ፀሐፊ ደግሞ 'ከግብፅ በፊት ስልጡንና ገናና ነበረች። ግብፅን ቅኝ ገዝታ 18 የኢትዮጵያ ነገሥታት ተፈራርቀውባታል። ...' ይላል። "መጽሐፉ ሀገራችን የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት መሆኗን በአደባባይ ካስመሰከረ በኋላ በዓለማቀፉ የአስትሮኖሚ ኅብረት የተሰጣትን ቦታ ይተነትናል ። "...ኅብረ ከዋክብት constellations ማለት በሰማይ ላይ የሆነ አይነት ቅርፅ የሚሠራ የከዋክብት ስብስብ ሲሆን ቅርጹም ከማይቶሎጂ ጋር በተያያዘ መልኩ የሰው፣ የእንስሳት ወይም ሕይወት የሌለው ነገር ሆኖ ሊገለጽ ይችላል። ዓለማቀፉ የአስትሮኖሚ ኅብረት በ1930 ዓ.ም ከ88 ኅብራተ ከዋክብት ውስጥ ሶስቱን ማለትም አንድሮሜዳን ፣ ካሲዮፒያንና ሴፌውስን በኢትዮጵያውያን ስም መዝግቧል።... አንድሮሜዳ የኢትዮጵያ ልዕልት ስትሆን፤ ካሲዮፒያን ደግሞ የኢትዮጵያ ንግስት ናት። ሴፌውስ ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉስ ነው ። ..."

**መጪው ዘመን ለኢትዮጵያ ብሩህ ነው !**

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

## የቡና ዕትብቱ

ኃይለማርያም ወንድሙ

ኢትዮጵያ የቡና ዕትብቱ የተቀበረባት ሀገር ናት ።የቡና ሥርና ምድር (መሠረት) እንዲሁም ባህል መገኛ ።በአፋን ኦሮሞ ቡነ ይባላል ።የደስታ ተክለወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ቡና የታወቀ ተክል የእንጨት ስም፤ ፍሬው ተቆልቶና ተወቅጦ ፈልቶ የሚጠጣ ።አንዳንድ ሰዎች ቡኖ በሚባል ቦታ ስለተገኘ (ኢሉ አባቦራ) ቡና /ቡነ ይሉታል፤ ፈረንጆቹ ግን በከፋ ስላገኙት ካፌ (ከፋዊ) ይሉታል ሲል ይፈታዋል ።በኢትዮጵያ ሀገረኛ የሆነው ቡና ንቁ ሆኖ ለመዋል እና ጊዜ ለማሳለፍ የሚጠጣ ብቻ አይደለም።ሥራን በንቃት፣ በትጋት ለመሥራት ፤ በእረፍት ዕለታት ለመዝናናት፣ ለማውጋት በማኅበራዊ ውይይት ችግርን ለመፍታት ይጠቀሙበታል ።

በኢትዮጵያ ቡና ላይ የተለያየ ጥናት ያካሔዱት መልካሙ ዓለማየሁ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ Ethiopian Highlands: home for Arabica coffee (September 2015) ባወጡት ጥናት በኢትዮጵያ የተረጋጋ የቡና ግብርና የተጀመረው ከ2ሺህ ዓመታት በፊት ነው ።ቡና ከባህር ወለል በላይ 550-2750 ከፍታ የሚበቅል ሲሆን፤የአረቢካ ቡና ግን ከ1500-2500mm ባለው ከፍታ ይበቅላል ።ኢትዮጵያ ከብራዚል ፣ቪየትናም፣ ኮሎምቢያና ኢንዶኔዥያ ቀጥሎ በቡና ምርት አምስተኛ ደረጃ ላይ ስትሆን በአፍሪካ ደግሞ ፊታውራሪ ነች ።

በሀገሪቱ አራት የቡና ምርት ዓይነቶች አሉ ።የጫካ፣ ከፊል የጫካ፣የጓሮ እና የእርሻ ቡና ናቸው ።የጫካ ቡና፤በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይ ባሌ፣ ምእራብ ወለጋ፣ ቤንች ማጂ፣ ከፊቾ ሸኪቾ፣ መቱና ጅማ ይገኛል ። የጫካ ቡና የአረቢካ ቡና ማዕከል ሲሆን፤ ከሀገሪቱ የቡና ምርት 10 በመቶ ይሆናል ።ከፊል የጫካ እና የጓሮ ቡና እያንዳንዳቸው የሀገሪቱን የቡና ምርት 35 በመቶ ይደርሳሉ ።የእርሻ ቡና ደግሞ በመንግሥት እና በባለሀብቶች የተያዙ ናቸው ።የመንግሥት 5 በመቶ ፣ጥቃቅን እርሻዎች 15 በመቶ ይደርሳሉ ።በነዚህ ከሚመረቱት 95 በመቶው ኦርጋኒክ ናቸው ።

በንግዱ የሚታወቁት ዋና የቡና ዝርያዎች አረቢካና ሮቡስታ ናቸው ።ሊበሪካ እና ኤክሴላ ቡና ተብለው የሚታወቁ ንዑስ ዝርያዎችም አሉ ።በቃናቸውና መዓዛቸው የሚወደዱ በሽታን ለመቋቋም ለመድኃኒትነት የሚጠቀሙበት የሚችሉ ከፍተኛ ጄኔቲክ የሆኑ፤ ከፍተኛ ምርትና ጥራት ያላቸው ቡናዎች አሉ ሲሉ መልካሙ ዓለማየሁ በጥናታቸው ጠቁመዋል ።

ቡና በዓለም በጣም ተፈላጊ የእርሻ ምርት ነው። በዓመት እስከ 14 ቢሊዮን ዶላር ያወጣል ።ኢትዮጵያን ጨምሮ 121 ሀገሮች ቡና ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ ወይም ገዝተው ዳግም ይሸጣሉ፤ከ165 በላይ ሀገሮች ምርቱን የሚገዙ ናቸው ።በማደግ ላይ ካሉ ሀገሮች 50ዎቹ በቡና ንግድ ላይ ያሉ ሲሆን፤ ከአፍሪካ 25 ሀገሮች በቡና ውጭ ንግድ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ይመራሉ ።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሕይወት ቡና ላይ የተንጠለጠለ ነው ።በዓመት በአማካይ ከ200ሺህ እስከ ሩብ ሚሊዮን ቶን የሚደርስ ምርት ሲመረት፤ከዚህ ውስጥ ግማሹ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል። ቡና መጠጣት ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ሕይወትን መጋራት ነው ።ቡና ከሌላው ጋር መጠጣት ማለት ሰላም ናችሁ ማለት ነው፤ ሲሉ መልካሙ ዓለማየሁ ባወጡት ጥናት ጠቁመዋል።

መሰንበት ገረመው ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባወጡት ጥናትም በኦሮሚያ ቡና ለቃና ብቻ ሳይሆን ለጤናም ተብሎ ይፈላ ነበር ።በብዛት ለራስ ምታት ሕመም ማገገሚያና ማከሚያ ይጠቀሙበታል ።በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል፤ ለሚያስቀምጣቸው ሰዎች እንዲሻላቸው ቡና በማር ተደርጎ ይሰጣቸዋል ።የቡና ሥነሥርዓቱ ልዩ ሚናው ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አብሮነትን በመፍጠር ማሳደጉ ነው ።በቡና ሥርዓት መሳተፍ የበጎ ዕድል ተምሳሌት፤ ሥርዓቱ የሃይማኖትና የብሔር ድንበር ሳይገድበው የማኅበረሰብ አብሮነትን ለመፍጠር ይረዳል ሲል ጥናታዊ ጽሑፉ ያስረዳል ።

መታሰቢያ ዮሴፍ ከአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ (A CULTURE OF COFFEE: TRANSMEDIATING THE ETHIOPIAN COFFEE CEREMONY April 26th, 2013) በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናትም ፤ የቡና ሥርዓቱ የማኅበረሰብ አብሮነትን በመፍጠር ያለውን ሚና ጠቅሰዋል።‹‹ ...የማኅበራዊ ሕይወት ማዕከላቸው ነው፤...እየታየ ያለው የጎጠኝነት ውጥረቱ እንዳለ ሆኖ፤ የጋራ የሆነው ባህላዊ የጀበና ቡና ሥርዓታቸው ብሔራዊ መለያቸው ነው።በማንኛውም ኢትዮጵያዊ



ቤት የምታገኙት ። በገጠራማ ጎጆ፣ በከተሞች ዘመናዊ ቤቶች።የቋንቋ፣ የእምነት፣ የአለባበስ ልዩነት ካልሆነ፤ በሁሉም ብሔር የምታገኙት ሥርዓት ነው።›› ይላሉ። ፓንክረስት ደግሞ በተለይ በኢትዮጵያ ባህል ውስጥ ከዓለም አቀፍ ውስብስብ ታሪካዊ ንግድ ጋር የተቆራኘ ፖለቲካዊና ሰብዓዊ መስተጋብር ያለው ነው ይሉታል ።

ዶን ሴማን አሜሪካን ኢትኖሎጂስት Coffee and moral order 2015 በሚል ባወጡት ጥናት ባህላዊው የቡና አፈላል ሥርዓቱ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ነው፤ በእሥራኤል ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችም (ፈላሻ) ቡና ከማነቃቂያ፣ ባህላዊ መለያና እንዲሁም ከማኅበራዊ መዋቢያ (social lubricant) በላይ ነው። ግጭቶችን የሚፈቱበት፣ ሥርዓትን የሚያሲዙበት ሞራል የሚገነቡበት መድረክ ነው ሲሉ ያስረዳሉ ።

ዲያስፖራውም አንዳች የሚሰበሰብበት ሁኔታ ካለና አመቺ ቦታ ካገኘ፤ ቡና በጀበና አፍልቶ፣ ጠጥቶ፣ ተጨዋውቶ ይሰነባበታል ።በዓረብ ሀገር ፣ በምዕራባውያን ያሉ ኢትዮጵያውያን ይህ የተለመደ ነው ።በለንደን ኢትዮጵያውያን ቡና አፍልተው ጭሳጭሱን እያጨሱ ሲጠጡ ሲጨዋወቱ ፖሊስ ጭሱን አይቶ በፍጥነት በአምቡላንስ መጣ፤ የሚቃጠል ነገር ያለ መስሏቸው ነው ።የኢትዮጵያ ባህል መሆኑን ተረድተው ተረጋግተው መመለሳቸውን ከቡናና ሻይ ልማት ባለሥልጣን ያገኘሁት መረጃ ያስረዳል ።እርግጠኛ ነኝ ቡና ጠጡና ሂዱ መባላቸውና ፖሊሶቹም መጠጣታቸው የማይቀር ነው፤ በሰው ሀገር ቢሆንም የቡና ሥርዓቱ ሀገርኛ ባህላቸው ነዋ።

ኢትዮጵያን የሠራት የቡና ሥርዓታችን ነው የሚለው ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም፤ ባንድ ወቅት ስለዚሁ ሲናገር ቡና የአንድነታችን ምስጢር የአብሮነታችን መሠረት ነው።ቡና ለሀገራችን ከሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በላይ ኢትዮጵያን በኅብረት በመተሳሰብ ላይ አርጎ የገነባበት አስተዋፅኦ ይበልጣል ።ስለዚህ ዛሬ የምናወራለት ማኅበራዊ ሕይወታችን አብሮነታችን መደጋገፋችን ማገር ሆኖ ያቆየው ያጠናከረው አሁን የያዘውን ቅርፅ የሰጠው ቡና እና የቡና አጠጣጥ ሥርዓታችን ነው ብሎ ነበር ።

ቡና የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት የጀርባ አጥንት ነው። ሀገርኛ ተወዳጅ ባህላዊ ሥርዓት። በዓልም ሲሆን አክብረው በልተው ጠጥተው ሲያበቁ፤ በቤቱ ቡና ካላፈሉ በዓሉ በዓል የማይመስላቸው ብዙዎች ናቸው ። ጎረቤት እንኳን አደረሰህ/ሽ ተባብሎ በዓሉን የሚያደምቀው ቡና በጋራ በመጠጣት ባህሉ ነው ።የቡና ሥርዓት ሐረር ብትሔዱ ጎንደር፣ ባሌ ብትሔዱ ቦሌ፣ ላሊበላ ብትሔዱ ጋምቤላ፣አሳይታ ብትሔዱ ወላይታ ፣ሰላሌ ብትሔዱ ሶማሌ፣ ሆሳዕና ብትሔዱ ቦረና ፤ ሲዳማ ብትሉ አዳማ፣አስመራም በሉት ሰመራ አይታጣም ።የቡና ሥርዓቱ የሚከናወንበት መንገድ በኢትዮጵያ በብዛት ተመሳሳይ ነው ።

እንግዳ ሲመጣ ማስተናገጃው ማጫወቻው ቡና ነው። የትም ብትሄዱ ፤ ‹ግቡና ቡና ጠጡ ›ነው የምትባሉት። ቡና እንግዶች የሚስተናገዱበት ትልቁ ግብዣ ነው። ሰዎችም በገጠር አካባቢ ሲያልፉ የሚተዋወቁ ከሆነ ሰላም ይባባላሉ፤ሰላም የተባለው ‹‹ ጎራ በሉና ቡና ጠጡና ትሄዳላችሁ ›› የሚል ግብዣ ይቀርብለታል ። በአፋን ኦሮሞም ጎርተኒ ቡነ ዱጋቲ ዴማካ? (ማል ኢንጎርተኒ? ቡነ ዱግተኒ ኢንደምተኒ? ) ፍቺው ምነው ጎራ አትሉም? ቡና ጠጥታችሁ አትሄዱም እንዴ? ማለት ነው ።መንገደኛም

በራፍ ላይ አረፍ ብሎ ቡና ጠጥቶ ይሄዳል ። ሁሉም በፍትሐዊነት በዴሞክራሲያዊነት የሚስተናገድበት ሀገርኛ ሥርዓት ።

ቡና ሲፈላ አቦል ፣ቶና (ሁለተኛ )፤ ሦስተኛ (በረካ) በየቤቱ የተለመደ ነው ።ጎረቤት ተሰብስቦ ማኅበራዊ ጉዳዩን ይወያይበታል ።ቤት ማሞቂያና ማድመቂያም ነው ።ሴቶች የቤት ሥራን የሚለማመዱት ቡና በማፍላት ነው ።በኢትዮጵያውያን ቢያንስ በቀን አንዴ እንኳ ቡና የማፍላት ልማድ አለ ።ሥርዓቱ ጊዜ ቢወስድም ፤ ሥነ ጥበባዊ ፣ ባህላዊ ነው ።የባህል መስተጋብር የሚፈጥር የብሔር፣ የጎሳ፣ የእምነት ድንበር የሌለበት ።

የቡና ዛፍ ተተክሎ ፍሬው ሲደርስ እሸቱ ተለቅሞ ከነገለፈቱ ተቆልቶ፤ በአንዳንድ ቦታዎችም የደረሰው ቡና ደርቆ ከነገለፈቱ ተቆልቶ ይጠጣል ።ቡና እጥረት ባለበት ቦታ ከገብስ ጋር ቀላቅለው ፤ቆልተው፤ ወቅጠው፤ አፍልተው መጠጣት የተለመደ ነው ።ቡና በቅቤ አፍልተው የሚጠጡም አሉ ።በተለይ በገጠር፤ ይህ ግን በዓል ሲሆን አልያም ግብዣ ሲኖር የሚደረግ ነው ።የቅቤ አጠቃቀም ሥርዓቱ ከቦታ ቦታ ይለያያል።አንዳንዶች ቅቤውን ሲኒ ላይ አድርገው ለታዳሚው ሲቀዱ ይታያል።የተነጠረውን ቅቤ እየፈላ ባለው ቡና ላይ በጀበና ጨምረው የሚጠቀሙም አሉ ።ይህ ግን ለወደዱት ቡናውን በቅቤ ሞላ ጎላ አድርገው ሲሰጡት፤ ላልፈለጉት ደግሞ በጀበና አጠቃቀም ዘያቸው ለስሙ ቅቤ የተደረገበት እንዲመስል አድርገው ይቀዱለታል።

በዓል ሲሆን ደግሞ ቡና በተደጋጋሚ ማፍላት የተለመደ ነው ።በዚህም ጎረቤት ተጠራርቶ ቡና በማፍላት እንግዶችን ማስተናገድ አለ ።ከቡናው ጋራ የቡና ቁርስ እንዳቅሚቲ ይቀርባል ።ዳቦ፣ ቂጣ፣ አምባሻ፣ ፈንዲሻ፣ ህብስት፣ አነባበሮ፤አልያም ቆሎ ወይም ንፍሮ ይዘጋጃል ።ካልሆነም እንጀራ ተቆርሶ በሚጥሚጣ ተደርጎ ለእድምተኛው ይቀርባል ።በዚህም የወግ የወጋቸውን ያወጋሉ ።በማወደስም ሆነ በመውቀስ ስለ አካባቢያቸው ሀገራቸው ጉዳዮች ያወራሉ ይጨዋወታሉ ።በኢትዮጵያ ቡናን በስኳር መጠጣት የከተሞች ልምድ ነው ።ወደ ገጠር ብትሔዱ ቡና ባዶው አልያም በጨው ይጠጣሉ፤እንጂ በስኳር የመጠጣት ፍላጎት እምብዛም የላቸውም ።ቡና በጨው፣በቅቤ እንዲሁም ከነገለፈቱ መጠጣታችን በሌላ ሀገር የለሌ ሀገርኛ ልምድ ነው ።

የጀበና ቡናችን አደባባይ እየወጣ ሴቶች ቡና እያፈሉ የሚውሉበት እየሆነ ነው ።አሁን አሁን በማሽን የተፈላ ቡና ሰው አታሰየኝ ያለ ይመስላል ።ሰው የማሽን ቡና የመጠጣት ስሜትም ሆነ ፍላጎቱ እየሳሳ ነው ።በዚህም ምግብ ቤቶች ሻይ ቤቶችና ቡና ቤቶች በረከቦታቸው ሲኒውን ደርድረው የጀበና ቡና ከሰል ላይ ጥደው የሚያፈሉበት ወቅት ላይ ደርሰናል ።ሰው የጀበና ቡና ዙሪያ ተኮልኩሎ ቡናውን ጠጥቶ ተጫውቶ ይሄዳል ።

እንደ እኛ ቡና አጠጣጥ ቢሆን ኖሮ፤ ያመረትነው ቡና እንኳን ወደ ውጭ ሀገር ልከን ልንሸጠው ለራሳችንም አይበቃንም ነበር ብዬ አስባለሁ ።አንድ ቡና አፍልተን እስከ ሦስተኛ ዙር የመጠጣት ባህላችን ቡናውን ቆጥበንም ለውጭ ምንዛሪ እንድናተርፍ የበጀን ይመስለኛል።መሰንበት ገረመው ከባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በጥናታቸው በኢትዮጵያ ቡና በጣም እንደሚጠጣ ሲጠቅሱ (...ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገሮች ኢትዮጵያ በጣም ቡና ተጠቃሚ ከሆኑት ቀዳሚዋ ሀገሮች አንዱዋ ናት ።ከሚመረተው ቡና ግማሽ የሚጠጋው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ነው ።...) ይላሉ ።እንደውም ከተቻለ ዙሩን እስከረውና እንጨምረው ።በሌሎች ሀገሮች እንዲህ

ዓይነት ልማድ የለም ።ወደ ምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች ግን ሻይን እንደ ኢትዮጵያው ቡና አንድ ጊዜ ጥደው ሦስት ዙር አፍልተው የመጠጣት ልምድ እንዳላቸው አንብቤያለሁ።የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ሻይ አፈላል ሥርዓታቸው ልክ እንደ ኢትዮጵያ ይመስላል በተለይ የጃፓን ።

የኢትዮጵያ ሴቶች በትውፊታዊ (Tradition) ዘዬ ይህን የቡና ሥርዓት ከቤተሰቦቻቸው ተቀብለውታል።ቡና በዓለም ብዙዎች ሊጠጡት የሚሹት ብቻ ሳይሆን የሚጠጡት ነው ።የብዙዎችን ልብና ቀልብ የሚስብ በዓለም ገበያም ሁነኛ ሚና ያለው ሲሆን ሀገራችንም ትልቁ የውጭ ምንዛሪ ምንጭዋ ነው ።(የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማት ባለሥልጣን ሰሞኑን ያወጣው መረጃ ፤ ሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና የውጭ ንግድ ኢትዮጵያ ከፍተኛውን ገቢ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር አግኝታለች፤ በጥራቱ አንደኛ ነጥብ ያመጣ አንዱ ኪሎ የኢትዮጵያ ቡና 884 ዶላር ተሸጧል) ።ይህም ቡና በባህልና በምጣኔ ሀብት በሀገራችን ያለውን ሚና ፤በዓለም በብዙዎች ሕይወት ውስጥ እንዴት ልዩ ቦታ እንዳለውም ጭምር ያሳያል ።

በርግጥም በሠርግ እንግዶች ተስተናግደው ተሰናብተው ሲያበቁ ፤ዘመድ አዝማድ ጎረቤቱ የደስታቸው ማሟሻ የሚያደርጉት ቡና ሲጠጡና ሲያወጉ ነው ። ኃዘንም ሲያጋጥምም ሰውን ቡና ማጠጣት በከተሞች ጭምር የተለመደ ባህል ነው ።ይህም የሚያሳየን በባህላችን ቡና ለደስታ መዝናኛ፣ ለችግርም ደግሞ መጽናኛ ሆኖ የሚያገለግለን ትልቅ ዕሴት መሆኑን ነው ። እናም ቡና በደስታም በኃዘንም ከየቤቱ የማይወጣ፣ የማይታጣ ሀገርኛ ሥርዓት ነው ።

ቡና ሲቆላ ምጣዱን፣ ሲፈላ ደግሞ ጀበናውን፣ሲቀዳ ረከቦቱንና ሲኒውን ስታዩት የሚሰጠው ስሜት አለ።ምንም ቡና ስሜት የለኝም ያለኝ አንድ ጎልማሳ ፤ ቡና ተፈልቶ ሲኒው ረከቦቱ ላይ ተደርድሮ ሳየው ቤቱ ሞቅ ደመቅ ያለ ይመስለኛል ደስ ይለኛል ብሎኛል ።በርግጥም የቡና ቁርሱ በቤቱ ውስጥና ረከቦቱ ዙሪያ የሚጎዘጎዘው ጉዝጓዝ (ቄጠማ፤ ሳር የመሳሰሉት) ቤቱን ጥሩ አድርገው እንዲያውዱ ጣል ጣል የሚደረጉት አሪቲና ጠጅ ሣር ፤ በር ላይ የሚጤሰው ዕጣንና ወይራ የቤቱን ግርማ ሞገስ የሚጨምሩ ጥሩ ጠረንና መዓዛ የሚፈጥሩ የቡናውን ታዳሚ ሐሴት የሚያጭሩ ናቸው ።ይህ የኢትዮጵያዊ ሁሉ ባህል ነው ።እንደቄጠማ የመሳሰሉ እርጥብ ነገሮች የሚጎዘጎዙት ለምለም ነገሮች ከመመኘት በመነጨ ነው ።

በአንዳንድ ቦታዎችም ቡናውን ከጠጡ በኋላ ከሲኒው ላይ የቀረውን አተላ አፍሰው የሕይወታቸውን ዕጣ ፈንታ በመገመት ይዝናኑበታል ።ቡና በሀገሪቱ ውስጥ የዕለት ተዕለት ኑሮ አካል እና ሕዝቦች በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በአኗኗራቸው፣ በአቋማቸው ወይም በልማዳቸው ቢለያዩም ወደ አንድነት በማምጣት ተወዳጅነት ያለው ነው። ለሀገሪቱ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ቡናን በኢትዮጵያ ውስጥ ሁነኛ ሚና ያለው ያደርገዋል።

ቡና የአካባቢ ነጋዴዎችን መተዳደሪያ ከመደገፉ ባሻገር የኢትዮጵያ ሕዝብ የማኅበራዊ ትስስር ዋና አካል ነው። ከላይ እንደገለጽነው የቡና ሥርዓት በኢትዮጵያ ዘወትር የሚከወን ነው ።ሰው በምድጃው ዙሪያ ተሰባስቦ ቡናውን እየጠጣ ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ይወያያል፤ ይቀላለዳል፣ ወግ ያወጋል፣ በሽሙጥም ይዋጋል፣ሥራው፣ጤናውን ሁሉ ያወራል፤ ችግሮችን ይፈታበታል ።የተጣሉን ያስታርቅበታል እንግዳን ይጋብዝበታል ፤ዜናዎችንና መረጃዎችን ይጋራል ።

አንዳንድ መረጃዎች የቡናው ሥነ-ሥርዓታችን ሙሉ የስሜት ህዋሳት ተሞክሮ የሚያካትት ነው ይላሉ ።ማየት፣ መስማት፣ መዳሰስ፣ መቅመስ፣ እና መስማት የሚባሉት አምስቱ የስሜት ሕዋሳት የሚታይበት መጠጥ ቡና ነው ።የሚባለው በሀገራችን ባህል ቡናው ተቆልቶ ሲጨስና እንዲሁም በሙቀጫ ሲወቀጥ በጀበና ሲፈላ ጠስ ጠስ ሲል ስንሰማው ሲቆላ ስናየውና ስንዳስሰው፣ የቡናው መዓዛ በሽታው ሲያውደን ፣ ተፈልቶ ቀምሰን እየጠጣን ቃናውን ስናጣጥመው ነው ።

ከላይ እንደገለፅነው ሀገርኛው የቡና ሥርዓት የሰርከ ክስተት ነው ።የምጣኔ ሀብቱን የአንበሳ ድርሻ የያዘ ነው ።በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው ግን ትኩረት የተሰጠው አይመስልም፤ የቡና ሥርዓታችን ለብቻው የቱሪስት መስህብ ነው።ቱሪዝም ኮሚሽን ፖስተር በሚያሳትምበት ጊዜ የወለጋዋ ውቢት ኢትዮጵያ ጥበብዋን ለብሳ ቡና በጀበና እያፈላች የሚያሳይ ፎቶ አስታውሳለሁ።በሀገር ውስጥም ለገበሬው ለነጋዴው ለወዛደሩ ለሹፌሩ የገቢ ምንጭ ነው ።እናም ‹ምሉዕ በኩልሄ› ግልጋሎት ለሚሰጠን ቡና ትኩረት እንስጠው፤ገበሬው ቡና በማምረት ላይ እንዲተጋ ይደረግ፤በገቢው እየተበረታታ የበለጠ እያመረተ ምንዛሪ ያመጣልን ።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በክረምት ብቻ ለምን?

**አስናቀ ፀጋይ**

የ2014 ዓ.ም የክረምት ወራት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በአስራ አንድ የተለያዩ ዘርፎች በሁሉም ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችን በማሳተፍ ከሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሲከናወን ቆይቶ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ፍፃሜውን አግኝቷል፡፡

ሲከናወን በቆየው በዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መንግስትና ህብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉትን 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ለማዳን ታቅዶ 14 ቢሊዮን ብር ማዳን ተችሏል፡፡ አገልግሎቱም 40 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች ተደራሽ ሆኗል፡፡

የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አሰጣጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት እንዲኖረውና በቀጣይ በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ለማስቻል የፌደራል ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ብሔራዊ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲና የአሰራር ማዕቀፍ እያዘጋጀ ይገኛል፡፡

ፖሊሲና የአሰራር ማዕቀፍ ከማዘጋጀት በዘለለ ታዲያ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በክረምት ብቻ ሳይሆን በበጋ ወቅትም ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ብዙዎች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ለዚህም ወጣቱ በበጋ ወቅት ከሚያከናውነው የግል ስራና ትምህርቱ በተጓዳኝ በትርፍ ጊዜው እውቀቱን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማዋል እንዳለበት ይታመናል፡፡

ወጣት ፋጡማ ሃሰን አርሲ ሮቤ ተወልዳ ያደገች ቢሆንም ኑሯዋ አዳማ ከተማ ነው፡፡ በከተማው በክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር ውስጥ በመታቀፍ የአቅመ ደካማ ቤቶችን በማደስ፣ ጎዳና ላይ የወደቁ ልጆችን በማንሳትና በመደገፍ በሌሎችም የበጎ ፍቃድ ስራዎች ላይ ስትሳተፍ እንደቆየች ትናገራለች፡፡


‹‹ብዙ ጊዜ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መስጠት የተለመደው በክረምት ወቅት ነው›› የምትለው ወጣት ፋጡማ፤ በነዚህ ጥቂት ወራት አገልግሎቱን ለበርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ ስለማይቻል አገልግሎቱን በበጋ ወቅትም ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ትናገራለች፡፡ ወጣቱም ከትምህርትና የስራ ግዜው ላይ ትርፉን ለዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማዋል እንደሚገባው ታስረዳለች፡፡

ለዚህም ይህን ዘርፍ የሚመሩ የመንግስት አካላትና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ስራውን ሊደግፉና ሊያበረታቱ እንደሚገባ ታመለክታለች፡፡ በተመሳሳይ ባለሀብቶችም ወጣቱን ከጎን ሆነው ቢደግፉ አገልግሎቱን በስፋት መስጠት እንደሚቻልም ነው ወጣት ፋጡማ የምታስረዳው፡፡ ይህም በክረምቱ ወቅት ያልተፈቱ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን ችግር ለመፍታት እድል እንደሚሰጥ ትጠቁማለች፡፡

ወጣት ኤልሳ ኃይለ መስቀል የቀድሞው የኢትዮጵያ የሴቶች እግር ኳስ ቡድን ተጫዋች ስትሆን፤ ከአማራ ክልል ደብረ ብርሃን ከተማ አፄ ዘርዓያእቆብ ክፍለ ከተማ እንደመጣች ትናገራለች፡፡ የደብረ ብርሃን ከተማ የሴቶች እግር ኳስ ክለብን ከማሰልጠን ውጪ ሙሉ ጊዜዋን ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመስጠት እየሰራች እንደምትገኝም ትገልፃለች፡፡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱን ከአስር አመት በፊት እንደ ጀመረችም ታስረዳለች፡፡

በክረምት ወቅት በደብረ ብርሃን ከተማ ሲከናወን የቆየውን የክረምት ወቅት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በተለይ ደግሞ ከህልውናው ዘመቻ፣ ከደም ልገሳ፣ ከአረጋውያን ቤት ጥገና ጋር በተያያዘ ያለውን ስራ በማስተባበርና በመሳተፍ ላደረገችው አስተዋፅኦ ከፌዴራል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሽልማት እንዳገኘችም ትጠቁማለች፡፡

ከሴቶች ጋር በተገናኘ በከተማዋ ከልጅነቷ ጀምሮ በርካታ ስራዎች ስትሰራ እንደነበርና ሴቶች በስፖርት በተለይ ደግሞ በእግር ኳስ ተሳታፊ እንዲሆኑ ስትሰራ መቆየቷን ተናግራ፤ ሽልማቱ የእርሷ ብቻ ሳይሆን



ወጣት ብሩክ መስሰ፤

በምትኖርበት አካባቢ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ስራ ለተሳተፉ ሁሉም ወጣቶች መሆኑንም ትገልፃለች፡፡

እርሷ በትኖርበት አካባቢ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በክረምት ብቻ ሳይሆን በበጋም ጭምር እንደሚሰጥ ትናገራለች፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ የክረምቱን ያህል እንዳልሆነና በበጋ ሰፊ ጊዜ ስለሚኖር ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ትጠቁማለች፡፡ በጎነት ለራስ እንደመሆኑ ወጣቱ በክረምት ወቅት ብቻ ሳይሆን በበጋ ወቅትም የበጎ ፍቃድ ስራዎችን ማከናወን እንዳለበትም ታመለክታለች፡፡ ከዚህ አኳያ እርሷ በምትኖርበት የደብረ ብርሃን ከተማ አፄ ዘርያእቆብ ክፍለ ከተማ የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በበጋውም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ታስረዳለች፡፡

በክረምት ወቅት ትምህርት ስለሚዘጋ አብዛኛውን ወጣት ማግኘት የሚቻለው በዚሁ ወቅት በመሆኑ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱን በበጋ ወቅት በስፋት ለመስጠት ችግሮች እንደሚያጋጥሙም ወጣት ኤልሳ ጠቅሳ፤ በበጋ ወቅት የወጣቱን በጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳታፊነት ለማሳደግ ከወዲሁ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ እንዳሉም ታብራራለች፡፡

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚቋረጥ ባለመሆኑና ሁሌም ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ሁሉም ወጣት ትርፍ ጊዜውን ለዚህ በጎ ተግባር ማዋል እንዳለበትም ትምክራለች ወጣት ኤልሳ፡፡ ይህም የበርካታ ህብረተሰበ ክፍሎችን ህይወት የሚያሻሽል መሆኑም ትጠቁማለች፡፡

ወጣት ብሩክ መሰለ የኢትዮጵያ ስካውት ማህበር ስራ አስፈፃሚ ኮሚሽነር ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት የሚገኝባት ሀገር እንደመሆኗና የክረምት የበጎ ፋቃድ አገልግሎት ደግሞ የሚሰጠው ለጥቂት ወራት በመሆኑ በበጋ ወቅትም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ይህም በክረምት ወቅት የተከናወነውን አገልግሎት በእጥፍ በማሳደግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ማሳደግ ያስችላል፡፡

ከዚህ አንፃር በመንግስት አካባቢ ያሉ የሚመለከታቸው አካላት በክረምት ወቅት ሲሰሩበት በነበረው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት በበጋ ወቅትም ስራውን ማከናወን ከቻሉ ወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱን ለመስጠት ወደኋላ አይሉም፡፡ በመንግስት በኩል ያለው ሀብት ውስን በመሆኑና ሁሉንም የህብረተሰብ ችግሮች መፍታት የማይችል በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት ወጣቶች በያሉበት አካባቢ አቅማቸው የፈቀደውን አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ በክረምት ወራት



ወጣት ፋጡማ ሀሰን፤

የነበራቸውን ተነሳሽነትም አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

በርግጥ የበጋ ወራት የትምህርት ወቅት ቢሆንም ትምህርትን ጠንክሮ መማር በራሱ አንዱ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ነው፡፡ ከመደበኛ ትምህርት ውጪ ከፍተኛ የወጣቶች ቁጥር በመኖሩ ይህ ወጣት በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ እያንዳንዱ ችግሮች አቅም በመፈቀደ ሁሉ የሚችለውን ሁሉ ካደረገና ካስተባበረ በርካታ የማህበረሰብ ክፍሎችን መጥቀም ይቻላል፡፡

ወጣቶች ለማንኛውም ማህበራዊ ጉዳዮች ግንባር ቀደም ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡ በስካውት ማህበርም እያንዳንዱ አባል የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ የስካውት አንዱ መርህም በቀን ቢያንስ አንድ መልካም ተግባር መስራት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በስካውት ማህበር በክረምት ብቻ ያልተወሰነና በማንኛውም ጊዜና በእለት ተእለት ህይወት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ሌሎችም ወጣቶች በክረምት ብቻ ሳይሆን በበጋም ጭምር ከተለመደው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መስኮች በተጨማሪ ሌሎች ፈጠራ የታከለባቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዋናው ትርፉ የህሊና እርካት ማግኘት በመሆኑ አቅም በፈቀደ ሁሉ ከሁሉም ወጣት ተግባሩን መፈፀም ያስፈልጋል፡፡

ወጣት ብሩክ እንደሚገልፀው፤ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ የስካውት እንቅስቃሴ አለ፡፡ መንግስት ባስቀመጣቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዘርፎች ማለትም የአካባቢ ፅዳት፣ ችግኝ ተከላ፣ ማእድ ማጋራት፣ የሆስፒታል ውስጥ አገልግሎት፣ የቤት ማደስና ግንባታ ላይ ስካውቶች በንቃት በያሉበት አካባቢ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሴቶች የወር አበባ መጠበቂያ፣ በሰላምና በግጭት ተፈናቃዮች ዙሪያ ፈጠራ የታከለባቸው የበጎ ፍቃድ ስራዎችን አከናውነዋል፡፡

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደሚገልፁት፤ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ የወጣቶችን ሁለገብ ተሳትፎ ለማጎልበትና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ ወጣቶች ካልባሌ ቦታዎች በመራቅ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን ተጠቅመው እንደየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ፣ እንደህብረተሰቡ ፍላጎት በመንግስትና



ወጣት ኤልሳ ኃይለመስቀል፤

በማህበረሰቡ ያልተሸፈኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክፍተቶችን ለመሙላት ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ይገኛል፡፡

የዘንድሮው የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ‹‹በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ›› በሚል መሪ ቃል ሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም በይፋ መጀመሩን ተከትሎ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሁሉም ክልሎችና ከሁለቱም የከተማ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር አጠቃላይ ሂደቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ በበላይነት ሲያስተባብር ቆይቷል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃም በ2014 ዓ.ም የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት 19 ሚሊዮን ወጣቶችን ለማሳተፍ አቅዶ በሰራው ንቅናቄ 19 ሚሊዮን 800 ሺ ወጣቶችን በማሳተፍ የእቅዱን 105 ከመቶ ማከናወን ችሏል፡፡ በወሰን ተሻጋሪ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በወጣቶች ዘንድ ሀገራዊ አንድነት እንዲፈጠርና ትስስሩም እንዲጠናከር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

በበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ 40 ሚሊዮን የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ እቅድ ተይዞ ከ42 ሚሊዮን በላይ ያህሉ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተሰጠው የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም በመንግስትና በህዝብ ሊወጣ የነበረውን 12 ቢሊዮን ብር የሚገመት አገልግሎትን ለማዳን ታቅዶ 14 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ያህሉን ማዳን ተችሏል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ በዚሁ የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳትፈው ውጤታማ ስራዎችን ያከናወኑና ለመርሃግብሩ መሳካት አስተዋፅኦ ያደረጉ ወጣቶች እውቅናና ሽልማት መሰጠቱ በቀጣይ አገልግሎቱ በተጠናከረ መልኩ በበጋ ወቅትም ጭምር እንዲቀጥል መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡

ውድ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን ሳይሰስቱ ለውጥ በሚያመጡና ጠቃሚ በሆኑ ተግባራት ላይ በማዋል የድርሻቸውን ሲወጡ የነበሩ የበጎ ፍቃድ አምባሳደሮችና ሁሉም የበጎ ፍቃድ ወጣቶች በቀጣይ በርካቶችን ከጎናቸው በማሰለፍ በወሰንና በወራት፣ በባህልና በተለያዩ ሁኔታዎች ሳይገደቡ በየመስኩና በየአቅጣጫው የጀመሯቸውን ሰብአዊ አገልግሎቶች ከክረምቱ ባሻገር በበጋውም ወራት ይበልጥ አጠናከረው ማስቀጠል ይጠበቅባቸዋል፡፡

# የምድር በረከት

## የከበሩ የጌጣጌጥ ማእድናት ግብይት ክለሳ- የዘርፉ ባለሀብቶች ተቆርቋሪነት

ስምስም መንግሥቱ

አምራች፣ አዘዋዋሪና ላኪዎችን (ኤክስፖርተር) በአንድነት አጣምሮ የሚይዘው የጌጣጌጥ ማዕድን ዘርፍ ሰፊ ቁጥር ያለው ኃይል በማሳተፍ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነው። በዚህ ረገድ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ለዓለም ገበያ ቀርቦ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ከፍ ያለ ድርሻ ያለው ነው ።

በዓለም ገበያ ላይ በህብረ ቀለማቸው ተፈላጊና በዋጋቸውም ውድ ከሆኑት የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናት መካከልም ኦፓል፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ ።የእጅ ጥበበኞች ደግሞ በቅርጽ ማውጫና በተለያየ የመስሪያ ማሽን በመታገዝ አስውበዋቸው ለጣት ቀለበት፣ለአንገት ሀብል፣ ለጆሮ ጉትቻ፣ ለእጅ አምባር፣ ለእግር አልቦ ጌጣጌጥ እንዲውል በማድረግ አገልግሎታቸውና ጥቅማቸው ከፍ እንዲል ያደርጓቸዋል። እሴት ተጨምሮበት ለገበያ ሲቀርብ ዋጋቸውም የበለጠ ከፍ ስለሚል የሚገኘው ገቢም እንዲሁ ይጨምራል፡፡

ኢትዮጵያ የምድር ውስጥ ፀጋ የሆኑ ከላይ ያነሳናቸው ማእድናት ሀብቶች ባለቤት ነች። አገሪቱ ከዘርፉ እየተጠቀመች ቢሆንም በሚፈለገው ያህል የውጭ ምንዛሪ ገቢ እያገኘችበት እንዳልሆነም ግን የዘርፉ ባለሙያዎች ደጋግመው ያነሳሉ ።በዘርፉ በተለያየ የሥራ መስክ ከተሰማሩት በሀብት የበለፀጉት ጥቂት ብቻ እንደሆኑ ይነገራል ።ማዕድን ለማልማት በምርት ሂደት ወቅት በሚፈጠር የጥራት መጓደል፣ ህገወጥ ግብይት፣ በገበያ ላይ የመደራደር አቅም ውስኑነት፣በጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርአት አለመመራት ከምክንያቶቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ዘርፉ ለሙስና የተጋለጠ መሆኑ ሌላው ተግዳሮት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ ።በጥብቅ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ካልተመራ ተጋላጭነቱን መቀነስም ሆነ ማስቀረት አይቻልም፡፡በዚህ ረገድ መንግሥት የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል ።እየሰራም ይገኛል ።ይህም ሆኖ በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችንና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ሙሉ ለሙሉ መቅረፍ አልተቻለም ።ለውጥ እስኪመጣ ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል ግድ ሆኗል ።

የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይትን በተመለከተ የማዕድን ዘርፉን የሚመራው ማዕድን ሚኒስቴር ከዛሬ ሶስት ወር በፊት የማሻሻያ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል ።ማሻሻያው በኦፓል፣ሳፋየርና ኤመራልድ የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በእነዚህ ዘርፎች የግብይት ሰንሰለትን ለማቃለልና ሀገርም ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ገቢ እንድታገኝ ያለመ ነው። ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረውን በመንግሥት የወጣ ወይንም የተቀመጠ የመሸጫ ዋጋ ተመንና ደረጃ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መስፈርቶች ተነስተዋል። ይህንን አስመልክቶ የንግድ ሥርአቱ በገበያ ብቻ የተመራ እንዲሆን መወሰኑን፣ ውሳኔው በአዋጅና መመሪያ የተደገፈ ስለመሆኑ በዚሁ አምዳችን ላይ ማቅረባችን የሚታወስ ነው ።

በማሻሻያው ውስጥ ከተካተተው መካከል ደረሰኝ አለመጠየቅ አንዱ ሲሆን፣ሌላው የማሻሻያ እርምጃ የይለፍ ሰነድ ደብዳቤ መያዝን ያስቀረ ነው። የማዕድን ሚኒስቴር ባለሙያዎች (ኤክስፖርተሮች) ልየታ አድርገውበት የዋጋ ውሳኔ ይሰጡበት የነበረውን አሰራርንም አስቀርቷል ።ላኪው (ኤክስፖርተሩ) ቀደም ሲል በነበሩ አሰራሮች ውስጥ ሳያልፍ ግብይቱን እንዲያካሂድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳለፈው ውሳኔ መተማመን ላይ የተመሰረተ ግብይት እንዲካሄድ ያስቻለ ነበር ።በወቅቱም ይህንኑ መሠረት በማድረግ አንዳንድ ላኪዎችን አነጋግረን በማሻሻያ ውሳኔው መሠረት ላኪው የሸጠበትን ትክክለኛ ዋጋ ካልገለፀ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚያውቅበት መንገድ እንደሌለና ይህም ሀገርን ተጠቃሚ እንደማያደርግ ነበር ሃሳብ የሰጡት፡፡

የማሻሻያ እርምጃው ከተወሰደ ከሶስት ወር በኋላ ግን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አሰራሩን በመፈተሽ ግብይቱ በተደረገው ማሻሻያ መሠረት እንዲቀጥል ሳይሆን፣ከማሻሻያው በፊት ይከናወን በነበረው የግብይት ሥርአት የመሸጫ መነሻ ዋጋ እንዲቀመጥ ክለሳ አድርጓል፡፡ሚኒስቴሩ ይህንኑ ውሳኔውን ከነምክንያቶቹ ሰሞኑን በዘርፉ ላይ በተለያየ ሥራ ከተሰማሩትና



በጌጣጌጥ ማዕድን ግብይት ላይ በተደረገው የማሳሻያ ክለሳ ውይይት ሲካሄድ፤

ዘርፉን ለሚመሩት የክልል የሥራ ኃላፊዎች ለውይይት በማቅረብ ምክክር አድርጓል፡፡ሚኒስቴሩ እንደገለጸው፤ በሶስት ወራት የማሻሻያ ጊዜያቶች ውስጥ በተከናወነው ሥራ መልካም የሚባሉ ጥሩ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ትልቁ ውጤት የሆነው ገቢን ማሳደግ ወይንም ከፍ ማድረግ ላይ ግን ድክመት ታይቷል ።እንደገና መከለስ ያስፈለገውም በዚህና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ነው። በማሻሻያው ጊዜያቶች ከፍተኛ መጠን ያላቸው የኦፓል፣ሳፋየርና ኤመራልድ የማዕድን ጌጣጌጦች ለዓለም ገበያ ቀርበዋል ።በዚህ ወቅት የላኪዎች ቁጥርም ጨምሯል ።አሜሪካን፣ታይላንድ ሀገሮችን ጨምሮ የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትም ተችሏል ።እንዲህ ያሉ መልካም ውጤቶች ቢመዘገቡም ከሽያጩ የተገኘው ገቢ ግን በዚህ ልክ አልሆነም ። ያለመጣጣም ክፍተት ተፈጥሯል።መነሻ የመሸጫ ዋጋ አለመኖር ወይንም አለመቀመጡ የፈጠረው ችግር እንደሆነም በሚኒስቴሩ ጠቅሷል። ይህን ክፍተት ለመሙላትም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን የመሸጫ መነሻ ዋጋ ለውይይት አቅርቧል፡፡ በገበያ የመወዳደር አቅም አለመፈጠሩንም በሌላ በኩል ሚኒስቴሩ ገልጿል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዳግም በከለሰው የማዕድን ጌጣጌጦች ግብይት ኦፓል በኪሎ ግራም 150 ዶላር፣ ሰሜን ሸዋ ራፍ ኦፓል በኪሎ ግራም 50 ዶላር፣ ክሪስታል ኦፓል በኪሎ ግራም 80 ዶላር፣ ፖሊሽ ኦፓል በኪሎ ግራም 1000 ዶላር፣ ራፍ ኤመራልድ በኪሎ ግራም 1000 ዶላር፣ ራፍ ሳፋየር በኪሎ ግራም 1000 ዶላር በሚል ያስቀመጠውን መነሻ የመሸጫ ዋጋ ለውይይት አቅርቧል ።በሚኒስቴሩ የቀረበውን መነሻ መሸጫ ዋጋ ጥቂት የሆኑት የውይይቱ ተሳታፊዎች ቢቀበሉትም ጠንካራ የመከራከሪያ ሃሳብ ባቀረቡ የውይይቱ አንዳንድ ተሳታፊዎች እንደገና እንዲታይ ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት በኤመራልድ፣ በሳፋየርና በኦፓል የማዕድን ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ፈቃደኛ የሆኑ ላኪዎች ከሚኒስቴሩ ጋር በመሥራት የጋራ የሆነ የመነሻ ዋጋ እንዲወጣ በማድረግ ከየዘርፉ ፈቃደኞች እንዲመረጡ አድርገዋል ።የተመረጡት ላኪዎችም ውይይቱ በተደረገ ማግስት ጠዋት በሚኒስቴሩ እንዲገኙ ጥሪ አድርገውላቸዋል፡፡በጥሪው መሠረት ተገኝተው ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ግን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያስቀመጠው መነሻ የመሸጫ ዋጋ ተግባራዊ እንደሚሆን ነግረዋቸዋል፡፡

በዕለቱም የመነሻ የመሸጫ ዋጋ ማሻሻያውን በተመለከተ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጋራ ለመወሰን ያቀረበውን ጥያቄ ፍቃደኛ ሆነው ከተቀበሉት መካከል አቶ ዓለምነህ የሻነህ አንዱ ነበሩ ።አቶ ዓለምነህ የጌጣጌጥ ማዕድን ለውጭ ገበያ በማቅረብ በሥራው ላይ የቆዩ ኤ ዋይ ኤስ ኤስ ፕሪሺየስ ስቶን ኤንድ ጁለሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ባለቤት ናቸው ።አቶ ዓለምነህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዳግም የማሻሻያ እርምጃ ለማድረግ ስለተገደደበት ጉዳይና በማሻሻያ ትግበራው ወቅት ማን ተጠቀመ? ማንስ ተጎዳ? ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ቀድሞውኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የወሰደው የማሻሻያ እርምጃ በጥናት የተደገፈ ውሳኔ እንዳልነበር ተሰምቷቸው ነበር ።ቅሬታም ነበራቸው ።ዳግም ክለሳ እንደሚደረግም ጠብቀው ነበር ።እርሳቸው ከማሻሻያው በፊት የነበረውን የግብይት ሥርአት ነበር የሚደግፉት ።ማዕድናቱ ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት በኦፓል የማዕድን አይነት ብቻ ወደ ስድስት አይነት ደረጃዎች ወጥቶላቸው፣ መነሻ የመሸጫ ዋጋም ተቆርጦላቸው ነበር የሚሸጡት ።በዚህ የግብይት ሥርዓት ላኪውና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አንዳንድ ባለሙያዎች ከማዕድናት ደረጃ አወጣጥ ጋር በተያያዘ በስምምነት እንዲሰሩ እድል ፈጥሯል።ለሙስና መንገድ ከፍቷል በሚል እሳቤ ይህን ለማስቀረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ እንደተገደደ ነው ከውሳኔው የተገነዘቡት ።

አቶ ዓለምነህ የሚኒስቴሩን ሥጋት ይጋራሉ። ለሙስና መንገድ አይከፍትም ብለውም አልተከራከሩም። ከማሻሻያው በፊት የነበረው ገበያ የአንድ ኪሎ ግራም የኦፓል ማዕድን ዋጋ 200 ዶላር ነበር ።ይህ ትልቅ ዋጋ ነበር። በርግጥ የገበያ መነሻ ዋጋውን መሠረት አድርጎ ሲሸጥ የነበረው ህግን ተከትሎ ከማይሰራው ጋር ተጠቃሚነቱ ሲነጻፀር ላኪውንም ሀገርንም ተጠቃሚ ያደረገ አልነበረም ።ይህንንም ለማስቀረት ነበር ሚኒስቴሩ ማሻሻያ ለማድረግ የተገደደው ።ይሁን እንጂ የተሻለ ነው ተብሎ በሚኒስቴሩ የተወሰነው የማሻሻያ እርምጃ ከሀገር ተጠቃሚነት አንጻር ከፍተኛ ጉዳት ነው ያስከተለው። ገዥዎች የፈለጉትን ዋጋ እንዲወስኑ በማድረጉና ከላኪውም በሀገር ደረጃ የተቀመጠ የመሸጫ መነሻ ዋጋ ባለመኖሩ ለመከራከር እድል የለውም ።ላኪው የተሻለ ገበያም ቢያገኝ ግልጽ ሆኖ የሸጠበትን ዋጋ ማሳወቅ በእርሱ በጎፈቃደኝነት ላይ ነው የተመሰረተው። ይህ አሰራር የተወሰኑ ላኪዎችን ከገበያው እንዲወጡ አድርጓል፡፡

የዳግም ማሻሻያ ክለሳውን እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው ላኪ የሚፈልገው መሆኑን የሚናገሩት አቶ ዓለምነው ፤ ማዕድን አላቂ ሀብት በመሆኑ በአንድ ጊዜ ነፃ መለቀቅ የለበትም ።ሀገርን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ነው ግብይቱ መከናወን ያለበት፡፡እንደርሳቸው በዘርፉ ላይ የሚገኘው ዘርፉን በደንብ የሚያውቀው በመሆኑ በመሸጫ መነሻ ዋጋው ላይ ሊሳተፍ ይገባል ።

ከሶስት ወር በፊት የነበረውን የማሻሻያ እርምጃ በጥሩ ጎኑም በክፍተትም የነገሩን ሌላው አስተያየት ሰጪ የከበሩ ድንጋዮች ጌጦችና ቅርጾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ባለቤት አቶ ሄኖክ ግርማ ናቸው። ማሻሻያው ቀጣይነት እንደማይኖረው እምነቱ ነበራቸው ።ያም ሆኖ ግን ጥሩ ጎንም ነበረው ። በግላቸው ኃላፊነት ተሰምቷቸው በእቅድ እንዲመሩ አድርጓቸዋል ።ግብይቱም ጨምሯል። እንዲህ መልካም ጎን ቢኖረውም ገቢ ላይ ዝቅተኛ ዋጋ መመዝገቡ ሀገርን የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል ።ዋጋ ተቀባይ መሆናችን ጎድቶናል የሚሉት አቶ ሄኖክ፤ መነሻ የመሸጫ ዋጋ ባለመኖሩ ገዥዎች በወረደ ዋጋ ለመግዛት ዕድል ፈጥሮላቸዋል ።ገዥ ደንበኞች ማዕድኑን በብዛት ገዝቶ ማከማቸት ነው የተያያዙት ።ላኪውም ከብዛት አገኛለሁ በሚል በተሰጠው የወረደ ዋጋ ለመሸጥ ተገዷል። በድካም ውስጥ አልፎ የተገኘን የማዕድን ሀብት ጥቅም እያገኙበት ያሉት ገዥ ሀገራት ናቸው፡፡የኢትዮጵያን የጌጣጌጥ ማዕድን በስፋት እየገዛች ያለችው ህንድ ናት። ከኢትዮጵያ በወረደ ዋጋ የገዙትን የጌጣጌጥ ማዕድን በተለያየ ኤግዚቢሽን ላይ በተሻለ ዋጋ ለዓለም ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ ሆነዋል ።አጠቃላይ በትምህርትና በእውቀት የተደገፈ የንግድ ክህሎት አለመኖርንም እንደ አንድ ክፍተት አቶ ሄኖክ አንስተዋል ።የመሸጫ መነሻ ዋጋ መኖር እንዳለበትም ያምናሉ ።

የማእድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ በዚሁ ወቅት በሰጡት ማሳሰቢያ መንግሥት በፖሊሲ፣በአዋጅና በተለያየ መንገድ ዘርፉን ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው። በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ እንዲገኙ ነገሮችን ያመቻቻል ። በተለይ አምራችና ላኪው ከዓለም አቀፉ ጋር የልምድ ልውውጥ ተሞክሮ እንዲያደርግ፣ ገበያውን እንዲያሰፋና የተለያዩ ዕድሎችን እንዲያገኝ አውደ ርእይና ኤክስፖዎችን በማዘጋጀት ያመቻቻል ።በዘርፉ ላይ የተሰማራው ባለሃብት ግን በንግድ መንፈስ በመንቀሳቀስ ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር እርሱንና ሀገርን ተጠቃሚ ማድረግ ይጠበቅበታል ።ያሉበትን ችግሮችንም ለመፍታትም ሆነ ከመንግሥት የሚፈልጋቸውን ድጋፎች ለማግኘት ጠንካራ የሆነ ማህበር በመመስረት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል ።ሰብሰብ ሲሉ ወይንም ሲደራጁ ለመንግሥት ድጋፍም አመቺ እንደሚሆንም ገልጸዋል፡፡

ሀገሪቱ ካለችበት ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ዘርፉ ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችንና ክፍተቶችን በተመለከተ በአንዳንድ የውይይቱ ተሳታፊዎች የቀረቡ ሃሳቦች ላይም ሚኒስትሩ ከዕለቱ አጀንዳ ጋር ተያያዥ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ በሌላ ጊዜ በሚዘጋጁ መድረኮች እንደሚወያዩባቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የእናት እውነት የልጅ ክብር ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ሊትዮጵ)**

ከእኔና ከእማዬ ማን እንደሚበልጥ በቅርብ ነው ያወኩት ። እማዬ እናቴ እንደሆነች የገባኝ ብዙ ዘግይቼ ነው ። ታላቅ እህቴ ነበር የምትመስለኝ ። ጡቷን እየጠባሁ አድጌ፣ በክንዷ ታቅፌ፣ በጀርባዋ ታዝዬም እናቴ አትመስለኝም ነበር ። መንገድ ላይ ከእናቴ ጋር ያየን መንገደኛ እህትማማች እንደሆንን ከማሰብ ባለፈ ምንም ነገር አስቦ አያውቅም ። በቁመት እኩል ነን..ከኔ የዘለለ.. እንደ እናት ሩቅ የሆነ ሀሳብ ስታስብ አይቻት አላውቅም። ግን በኔ ውስጥ የትም ቦታ ነበረች ። የትም ቦታ አገኛታለሁ። እሷ የሌለችበት ምንም ነገር አልነበረኝም። እኔም በእናቴ ሁሉም ቦታ አለው ። በእኔ ሁሉም ቦታ ውስጥም አለች ።

ሩሃማ ነው ስሜ..ሩሃማ ያለችኝ እናቴ ናት ። ምህረት የሚገባት ሴት ማለት ነው ። እናቴ እሷ በተራመደችበት የዘመን ሰርጥ ውስጥ እንዳልራመድ ስትል ነው ሩሃማ ያለችኝ ። እሷ ያየችውን የዘመን ነውር፣ የጊዜ ኩነኔ እንዳላይ ስትል ነው ሩሃማ ያለችኝ ። በእኔ ሩሃማነት ውስጥ የእሷ ያለፈ ታሪክ ሲታደስ አይቻለሁ ። እኔ ፊት እናቴ ሁልጊዜም አዲስ ናት ። በእኔ ኃጢያት..በእኔ መተላለፍ ልትቆሽሽ የማይገባሽ ነፍስ ነሽ ስትል ሩሃማ.. ምህረት የሚገባሽ ሴት አለችኝ ። የአባት እዳ ለልጅ እንደሚባለው የእናቴ የዘመን ጸጸቶች እኔ ላይ አርፈው እንዳያሰቃዩኝ ምህረት የሚገባት ሴት አለችኝ ።

እናቴ ታሪኳን ስትነግረኝ ምን ያክል ስህተት ብትሠራ ነው የዚህን ያክል ትላንትን የተጸየፈችው እያልኩ አስባለሁ። አንድ ቀን አስራ ሁለተኛ ዓመቴን ባከበርኩበት ሰልስት ድንገት በተኛሁበት ልብሴ በደም ረጥቦ አየሁት.. እየጮሁኩ ወደ እናቴ ሮጥኩ ። ትታደገኛለች ብዬ ሳስብ በእኔ መከራ ውስጥ እናቴ ስትስቅ አየኋት ። በእናቴ አዲስ ባህሪ ነፍሴ ተረበሸች..ሳላውቀው በእናቴ ላይ ተስፋ የቆረጥኩበት የመጀመሪያው ቀን ያን ቀን ነበር ። እናቴን ሳውቃት ተስፋዬ ነበረች ። ለእግሮቼ የወርቅ ምንጣፍ፣ ለክንዶቼ ጌጣም አልቦ፣ ለሴትነቴ ዘውድና ማዕረግ ስትሆን አይቻት አውቃለሁ ። በደም በጨቀየሁበት ያን ቀን ግን ሳቀችብኝ ። ሳቋ ብዙ አልቆየም..ፊቴ ተንበረከከችና አቀፈችኝ ። ለምን እና እንዴት እንደደማሁ ሳይገባኝና ሳይገባት ‹የኔ ቆንጆ አደግሽልኝ..› ብላ ጉንጮቼን በደስታ ሳመቻቸው ። ሁሉም ነገር ግራ ገብቶኝ ነበር ። ልብሴ ላይ ያለው ደም በየት በኩል እንዴት ሆኖ እንደመጣ ሳላውቅ የእናቴ በደስታ መፍነክነክ ጤንነቷን እንድጠራጠር አደረገኝ ።

ፊቷ ላይ አለቀስኩ..እናቴን ፈራኋት ። ያቀፉኝን ክንዶቿን፣ የሳመኝን ከንፈሯን ተጠራጠርኩት ። ለዘላለም ሲራራልኝ የነበረውን እናትነቷን ሰጋሁት ። እቅፏ ውስጥ እያለፉ ልሸሻት ስታገላት ‹የኔ ቆንጆ..ምንም አልሆንሽም እሺ...ይሄ ተፈጥሮ ላንቺና ለእኔ የሰጠችን ጸጋችን ነው› ብላ ድጋሚ ሳመችኝ ።

አሁንም አልገባኝም..ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም ። ራሴን ከእቅፏ ለማውጣት ተናነኳት ወደ ደረቷ ስባ ይበልጥ እያቀፈችኝ ‹እኔ እያለሁ አንቺ ምንም አትሆኚም..እኔ እያለሁ የሚጎዳሽ ክንድ የለም ። ሩሃማዬ ነሽ ። ነፍስሽ መጽናኛዬ ናት› አለችኝ ።

እናቴ እንደዛ ቀን ግራ ገብታኝ አታውቅም ። ምን እንደሆንኩ ትነግረኛለች ብዬ ስጠብቅ ምንም ባልመሰለው እናትነት እቅፏ ውስጥ አስቀረችኝ ። በተንበረከከችበት ወደ ላይ አንጋጣ አይኖቼን ፈለገቻቸው። አይኖቼን ስታስተውላቸው ቆይታ እንባ አቀረረች ። ለቅሶዋ አስፈራኝ..ከሳቋ መልስ መነፍረቋ የሆነ ነገር እንደሆንኩ እንዳስብ አደረገኝ ። ለቅሶዋ አስለቅሶኝ ጉያዋ ውስጥ ነፈረኩ ።

‹የኔ ቆንጆ ደስታ እኮ ነው የሚያስለቅሰኝ ። ስላደግሽልኝ..ሴት ስለሆንሽልኝ ደስ ብሎኝ እኮ ነው› አለችኝ እያለቀሰ በሚፈግ ፊት ። ተረጋጋሁ..ምንም እንዳልተፈጠረ ማሰብ ጀመርኩ ። ግን ልቤ እየፈራ ነበር ። ልቤ ውስጥ ያለውን አንድ መዐት ጥያቄ ተረድታ ብትመልስልኝ ስል በማሰብ ተረጋጋሁ ።

‹ልብስሽን የነካሽ ደም የጸጋ ደም ነው..

ከማለቷ ‹ምንም አልሆንኩም? አልታመምኩም? ስል በፈራ ስሜት ጠየኳት ።

‹ምንም አልሆንሽም..የማደግሽ..የመሰልጠንሽ ምልክት ነው ። ሴት ልጅ እንዲህ እንዳቺ ደም ሲደማት ለኃላፊነት፣ ለእናትነት እየተዘጋጀች ነው ማለት ነው ። እናም አሁን አንቺ እናት ለመሆንና ኃላፊነት ለመሸከም ተዘጋጅተሻል ማለት ነው› አለችኝ ።

አስራ ሁለት ዓመቴን ባከበርኩበት ሰልስት በተኛሁበት ያስደነገጠኝ ደም የልዕልና ምልክት እንደሆነ እናቴ ስትነግረኝ..ስለደሜ ለጓደኞቼ ለመናገር ቸኮልኩ ። ከአሁን አሁን ከእናቴ እቅፍ ውስጥ ወጥቼ ወደሚያንጃብቡብኝ ወንዶች በመሄድ በመሽኮርመም ሴት እንደሆንኩና ለእናትነት እንደተዘጋጀሁ ላበስራቸው ተጣደፍኩ ። እናቴ ግን እንዲህ አለችኝ ‹አሁን ተጠንቀቀሽ የምትኖሪበት እድሜ ላይ ነሽ ። ይሄ ደም የክብር ደም ነው። አለችኝ በደም ወደረጠበው ቀሚሴ እየጠቆመች ።

ከእናቴ አፍ አዲስ ነገር ሰማሁ ። እንባዋን አድርቃ ሳቋን አምቃ ለሴትነቴ እንግዳ የሆነ ነገር ትነግረኝ ጀመር ። ለራሴ አዲስ ሆኜ በእናቴ ፊት ራሴን አገኘሁት ።

‹ይሄ ደም የሴትነትሽ ጌጥ ነው ። የውበት፣ የአፍላነት አሸንክታብ ። በስሌት ከኖርሽ ወደነገ ያደርስሻል በስሜት ከኖርሽ ደግሞ ነገሽን ይቀማሻል ። ይሄ ደም አንቺን ጠንካራና አስተዋይ የሚያደርግሽ እንጂ የትም ለማንም ራሽን የምትገልጪበት አይደለም ። ይሄ ደም ለባልሽ መልካም ሚስት፣ ለልጆችሽ ጥሩ እናት የሚያደርግሽ የተፈጥሮ ቃል ኪዳንሽ ነው ። ይሄ ደም ከስሜት አርቆ በስሌት ፍኖት ላይ ወደነገሽ፣ ወደምትናፍቂው ሕልምሽ የሚያስጠጋሽ እንጂ ጠልፎ የሚጥልሽ እንዳይሆን ራስሽን ጠብቂ ። አለችኝ ።

በእናቴ ምክር ነፍሴ በልቤ ውስጥ ገለሞተች ። ሰንኮፌን እየጣልኩ እንደምትለኝ አይነት ሴት እየሆንኩ ራሴን አገኘሁት ። እናቴ ነግራኝ የምሸረው እውነት የለኝም ። በእኔ ውስጥ አለች የለ? በእሷ ውስጥም መኖር እፈልጋለሁ..ያላባራ የእናቴ አደራ ከአሳቤ አደናቀፈኝ ። ወደ ምክሯ ሸፈትኩ ።

‹ከዚህ ደም በኋላ አንቺን ሽተው፣ ውበትሽንና ሴትነትሽን ተመኝተው በውሸት አፍ የክብር ቀሚስሽን ለመግለብ በዙሪያሽ የሚያንጃብቡ ወንዶች ብዙ ናቸው። እኔ አንቺን በአስራ አንድ አመቴ የወለድኩሽ ሕይወትን የሚያስተምረኝ መምህር አጠገቤ ስለሌለ ነው። በዛ የመጀመሪያውን ደሜን ባየሁበት ልጅነቴ ውስጥ ሕይወትን የሚያስተምረኝ ሰው ቢኖር ኖሮ ከሕልሜ ርቄ በምንምነት ውስጥ አልገኝም ነበር ። አሁን አንቺም የምልሽን ስሚ..ከዚህ ደም ቀጥሎ ሌላ ሴትነት፣፣ሌላ ክብር አለሽ እዛ ክብርሽ ላይ እስክትደርሺ የማንም ሳትሆኚ የራስሽና የሕልምሽ ብቻ በመሆን እንድትኖሪ አደራ እልሻለሁ ። ያኔ ሩሃማዬ ትሆኛለሽ..ያኔ ያጣሁትን ክብሬን በአንቺ ውስጥ አየዋለሁ› ስትል ያልተሳመ ጉንጩን ሳመችኝ ።

በእናቴ መሳም ውስጥ ነፍሴ ያልተረዳችውን አንድ መዐት ጥበብ ሸመተች ። ነፍሴ የተመኘችው እውነት ይሄ ነበር ። ይሄ ደም የኃላፊነት ደም እንደሆነ ገባኝ..ከዛ ደም በኋላ እናቴ እንዳለችኝ ተጠንቅቄ መርገጥና ተጠንቅቄ መኖር ጀመርኩ ።

ከዛ ደም በኋላ ከእናቴ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋወኩ..

# ዓለም አቀፍ



## የኔቶ አባል ሀገራት ለዩክሬን ዘመናዊ ፀረ ሚሳኤል መሣሪያ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገለጹ

የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል ሀገራት ለዩክሬን የሚያደርጉትን ዘመናዊ ፀረ ሚሳኤል መሣሪያ ድጋፍ እንደሚያሳድጉ አስታውቀዋል። አባል ሀገራቱ ሩሲያ በዩክሬን ዋና ከተማ ኪዬቭ የሚሳኤል ጥቃት መፈጸሟን ተከትሎ ነው ዘመናዊ ፀረ ሚሳኤል መሣሪያ ድጋፍ ለማድረግ ነው ቃል የገቡት ።

የዩክሬን አጋር የሆኑ 50 ሀገራት በኔቶ ዋና ጽሕፈት ቤት ብራሰልስ ተገናኝተው በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መክረዋል ።ዩክሬን ታሪካዊ ባለችው ከዚህ ውይይት በኋላም የኔቶ አባል ሀገራት ዘመኑን የዋጁ ፀረ ሚሳኤል መሣሪያዎችን ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

በዚህ መሠረት አሜሪካ ብሪታኒያ፣ ካናዳ፣ ፈረንሳይ እና ኔዘርላንድስ ከፀረ ሚሳኤል በተጨማሪ የራዳር እና ሚሳኤል ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። ከዚህ ባለፈም በቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ የጀርመን ፀረ ሚሳኤል ዩክሬን መድረሱን ቢቢሲ በዘገባው አመላክቷል ።

ብሪታኒያ ከሚሳኤል መቃወሚያው በተጨማሪ ለመረጃ እና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶች የሚውሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን እንዲሁም ሌሎች ጦር መሣሪያዎችን እንደምትደግፍ አስታውቃለች ።ካናዳ በበኩሏ 34 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ሰው አልባ አውሮፕላኖች፣ ሳተላይትና ሌሎች ዘመናዊ ጦር መሣሪያዎችን ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባቷ በዘገባው ተመላክቷል ።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የኔቶ አባል ሀገራት ለዩክሬን የሚያደርጉትን የጦር መሣሪያ ድጋፍ እንዲያቆሙ በተደጋጋሚ ማሳሰባቸው ይታወሳል ።ይሁን እንጂ አባል ሀገራቱ የፕሬዚዳንት ፑቲንን ማሳሰቢያ ወደ ጎን በመተው ዩክሬን ራሷን ትከላከልበታለች የሚሉትን የጦር መሳሪያ ድጋፍ አጠናክረው ቀጥለዋል ።

ይህ የኔቶ አባል ሀገራት ድርጊትም የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት አድማሱን እንዲያሰፋ ሊያደርገው ይችላል የሚል ስጋትን ማጫሩን ኤፍቢሲ ዘግቧል ።

## ሰሜን ኮሪያ አሜሪካና ደቡብ ኮሪያን አስጠነቀቀች



ሰሜን ኮሪያ የኒውክሌር አቅሟን ለማሳየት ረዥም ርቀት ተወንጫፊ ክሩዝ ሚሳዔል ሙከራ በማድረግ አሜሪካና ደቡብ ኮሪያን አስጠንቅቃለች ። ሰሜን ኮሪያ የረዥም ርቀት ክሩዝ ሚሳኤሎችን ሙከራ አድርጌያለሁ ብላለች። የሀገሪቷ መሪ ኪም ጆንግ-ኡን በባህር ላይ 2 ሺህ ኪሎ ሜትር የሚምዘገዘጉ ሚሳኤሎች በተወነጨፈበት ወቅት በቦታው የተገኙ ሲሆን ፥"ትልቅ እርካታ"እንደተሰማቸው መግለጻቸውን የሰሜን ኮሪያ የዜና አውታር (ኬ ሲ ኤን ኤ) ዘግቧል።

በዚህ የሚሳዔል ሙከራ "ጠላቶቼ ግልጽ ማስጠንቀቂያ እየሰጠኋችሁ መሆኑን እወቁት" ብለዋል ኪም ።በቅርቡ አሜሪካና ደቡብ ኮሪያ የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ማድረጋቸውን ተከትሎ ሰሜን ኮሪያ ያደረገችው የረዥም ርቀት የክሩዝ ሚሳዔል ሙከራ ለዚህ ምላሽ እንደሆነ ነው ቲ አር ቲ በዘገባው ያመላከተው ።

ፒዮንግያንግ "የባላስቲክ ሚሳዔልን ያስወነጨፍኩት ለአሜሪካና ደቡብ ኮሪያ የጋራ ወታደራዊ ልምምድ አፀፋ ለመስጠት ነው" ብላለች ።

የሰሜን ኮሪያው መሪ አክለውም ፣ ሀገራቸው ማንኛውንም ወሳኝ ወታደራዊ ችግርና ጦርነትን በማንኛውም ጊዜ በቆራጥነት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የኒውክሌር ኃይሏን ማጠናከር አለባትም ነው ያሉት።

ፒዮንግያንግ ካለፈው የፈረንጆቹ መስከረም 25 ቀን ጀምሮ ሰባተኛ የሆነውን የባለስቲክ ሚሳኤል ባለፈው እሑድ ማስወንጨፏ የሚታወስ ነው።

የሀገሪቱ ገዥ ፓርቲም የአሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ የጋራ ወታደራዊ ልምምድ እስከቀጠለ ድረስ የሚደረገው የሚሳኤል ሙከራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ውሳኔ ማሳለፉ የሚታወስ መሆኑን የዘገበው ኤፍቢሲ ነው።

ይህን ተከትሎ ሰሜን ኮሪያ ካሳለፍነው ሳምንት ጀምሮ በተከታታይ የሚሳዔል ማስወንጨፍ ሙከራዎችን እያደረገች እንደሆን ይታወቃል።

# ስፖርት





# አፄዎቹ ወሳኙን የመልስ ጨዋታ ነገ በቱኒዚያ ያደርጋሉ

**ቦጋስ አበበ**

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የ2014 ሻምፒዮኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ በአፍሪካ ሻምፒዮንስ ሊግ ቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ በሱዳኑ አል ሂላል በደርሶ መልስ ውጤት ተሸንፎ ወደ ቀጣዩ ዙር ሳያልፍ መቅረቱን ተከትሎ ኢትዮጵያን በአፍሪካ መድረክ የሚወክለው የፋሲል ከነማ ብቻ ሆናል፡፡ በአፍሪካ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ እየተሳተፉ የሚገኙት አፄዎቹ የመጀመሪያውን ቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ አሸንፈው የሁለተኛውን ዙር ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታም ባለፈው እሁድ ባህርዳር ስታዲየም ላይ አድርገዋል፡፡

አፄዎቹ የቱኒዚያውን ክለብ ሴፋክሲያንን በሜዳቸው በገጠሙበት ያለፈው እሁድ ጨዋታ ካለ ምንም ግብ አቻ ቢለያዩም በመልሱ ጨዋታ ነገ ወደ ቀጣዩ ዙር የሚያሳልፋቸውን ውጤት ለማስመዝገብ ከቀናት በፊት ወደ ቱኒዚያ አቅንተዋል፡፡ አፄዎቹ በሜዳቸው ያደረጉትን ጨዋታ ማሸነፍ ካለመቻላቸው በተጨማሪ ምንም ግብ አለማስቆጠራቸው ወደ ቀጣዩ ዙር ማለፍ የሚያስችላቸውን እድል ያጠበበው ሲሆን በነገው ወሳኝ ፍልሚያም የማሸነፍ ወይም ግብ አስቆጥረው አቻ የመለያየት ግዴታ ውስጥ ገብተዋል፡፡ አሰልጣኝ ኃይሉ ነጋሽም ቡድናቸው በመጀመሪያው ጨዋታ የነበሩበትን ድክመቶች አስተካክሎ በነገው የመልስ ጨዋታ የሚፈለገውን ውጤት ይዘው ለመምጣት ጥረት እንደሚያደርጉ ከባህርዳሩ ጨዋታ በኋላ ለሶከር ኢትዮጵያ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

"በመልሱ ጨዋታ ያሉብንን ክፍተቶች አርመን የተሻለ ነገር ይዘን ለመምጣት እንጥራለን" ያሉት አሰልጣኙ የተጋጣሚያቸውን የጨዋታ ታክቲክ መሠረት ያደረገ ዝግጅት አድርገው ወደ ሜዳ ቢገቡም ቡድናቸው ያገኛቸውን አጋጣሚዎች ወደ ግብ መቀየር ባለመቻሉ ጨዋታው ዐለዐ እንደተጠናቀቀ ተናግረዋል፡፡



**የመጀመሪያውን ጨዋታ በአቻ ውጤት ያጠናቀቁት አፄዎቹ ነገ በመልሱ ጨዋታ ትልቅ ፈተና ይጠብቃቸዋል፣**

አፄዎቹ በሜዳቸው አሸንፈው የተሻለ ውጤት ይዘው ወደ መልሱ ጨዋታ ለመሄድ ጉጉት እንደነበራቸው ያስታወሱት አሰልጣኝ ኃይሉ፣ የነበራቸውን እድል ባለመጠቀማቸው በተጫዋቾች ስነልቦና ላይ የፈጠረው አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

‹‹ብዙ ጊዜ ተጫዋቾች አሸንፈን እዚህ ጨርሰን እንሄዳለን የሚል ጉጉት ስለነበራቸው የማጥቃት ዕድሉ ላይ ትንሽ የመቻኮል ነገሮች ነበሩ፡፡ መጀመሪያም ጎል መሳት ያገኘነውን አጋጣሚ ያለመጠቀም ደግሞ ትንሽ እየወረድን እንድንመጣ አድርጎናል፡፡ እነዚህን ስህተቶች አርመን ለቀጣዩ ጨዋታ የተሻለ ነገር ይዘን እንቀርባለን ብለን እናስባለን›› ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የሴፋክሲያን አሰልጣኞች ቡድን አባል የሆነው የሱፍ ከሬይ ለሶከር ኢትዮጵያ ከመጀመሪያው ጨዋታ በኋላ በሰጠው አስተያየትም፣ "ለቀጣዩ ጨዋታ ጥሩ ውጤት አግኝተናል፣ ጨዋታው ጥሩ ነበር ስፖርታዊ ጨዋነት የተሞላበት ጨዋታ የነበረ ሲሆን አቻ ወጥተናል። ለቀጣዩ ጨዋታ ጥሩ ውጤት አግኝተናል። በሁለቱም ቡድኖች በኩል ፉክክር የታየበት ፈታኝ ጨዋታ ነበር አቻም በቂ ውጤት ነው›› በማለት ተናግረዋል፡፡

አጼዎቹ ጠንካራ የቡድን ስብስብ እንዳላቸው የገለፁት የሱፍ ከሬይ በተለይ የባህርዳሩ ጨዋታ በሜዳቸውና በደጋፊው ፊት ፈታኝ እንደነበር በማስታወስ አፄዎቹ ላላቸው ብቃት ‹‹እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ›› ብለዋል፡፡

‹‹አስደናቂ ደጋፊዎች ናቸው። ሙሉ ደቂቃ ቡድናቸውን ሲያበረታቱ ነበር ስታዲየሙ ውስጥ ጥሩ ነበሩ። ሜዳውም ተመችቶናል በጣም ደስ ይላል ለጨዋታ የሚመች ሜዳ ነው። ስታዲየሙ በጣም ደስ ይላል ጥሩ ብቃት ያየንበት ጨዋታም ነበር ፤ ያለው ነገር ደስ ይላል›› ሲሉም ለአፄዎቹ ደጋፊዎችና ለባህርዳር ስታድየም አድናቆታቸውን ገልፀዋል፡፡ የሱፍ ከሬይ በባህርዳሩ ጨዋታ ውጤት ባይከፋም የነገው የመልስ ጨዋታ ቀላል እንደማይሆንም ተናግረዋል።

አጼዎቹ በእሁዱ ጨዋታ ወሳኝ የአማካይ ስፍራ ተጫዋቻቸው ሱራፌል ዳኛቸው ጉዳት ማስተናገዱን ተከትሎ በነገው የመልስ ጨዋታ እንደማይሰለፍና ከቡድኑም ጋር ወደ ቱኒዚያ አብሮ እንዳልተጓዘ ተረጋግጧል።

ሱራፌል በመጀመሪያው የእሁዱ ጨዋታ አስቀድሞ መጠነኛ ጉዳት አጋጥሞት ለጨዋታው የመድረሱ ነገር ሲያጠራጥር ቢቆይም በ59ኛው ደቂቃ ተቀይሮ በመግባት መጫወት ችሎ ነበር። ሜዳ ላይ መቆየት የቻለው ግን ሃያ ደቂቃ ብቻ ነበር። ቀኝ ታፋው ላይ ከባድ ያለ ጉዳት አስተናግዶ ተቀይሮ ሊወጣ ችሏል።


## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በአብክመ በሰ/ሸዋ/ዞን የአንፆ/ገ/ወ/ኢ/ል/ት/ቤት ግ/ፋ/ን/ብ/አስ/ቡደን አገልግሎት ለሚሰጣቸው ሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል

ሎት 1 የጽ/መሳሪያ

ሎት 2.ህንፃ መሳሪያ

ሎት 3. የፅዳት እቃ

ሎት 4 የእንስሳት መድሃኒት እና ቁሳቁስ

እቃዎች በየዘርፉ ንግድ ፍቃዳቸውን በሚጋብዛቸው መሠረት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈለጋል፡፡

**ስለዚህ በጨረታው ለመሣተፍ የምትፈልጉ**

1. ተጫራቾች ህጋዊና በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድና ከመንግስት የሚጠበቅባቸውን የዘመኑ ግብር የከፈሉና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. በጨረታው መወዳደር የምትፈልጉ የማይመለስ 50/ሃምሳ ብር በመክፈል ከ4 /2/2015 እስከ 18/ 2 /2015 ከቀኑ 4.00 ሰዓት ግ/ፋ/ን/አስ/ቡድን ቢሮ ቁጥር 6 ድረስ በመምጣት መግዛት ይችላሉ፡፡
3. የጨረታ ሰነዱ በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ ላይ እና ዋጋው መሙያው ላይ የድርጅቱን ማህተብና ፊርማ በግልጽ በማስቀመጥ ለዚህ በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይቻላል፡፡
4. የጨረታ ሳጥኑ 18 /2 /2015 ቀን 4፡01 ሰዓት ታሽጐ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸውን በተገኙበት በዚሁ ቀን 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፣
5. ተጫራቾች የጠቅላላ ዋጋ 2% የጨረታ ማስከበሪያ እና የጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደላቸው የታወቁ ባንኮች የሚሰጥ እንደ ተጫራቾቹ ምርጫ በጥሬ ገንዘብ /CPO/ ወይንም በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና በፖስታው ውስጥ አሽጐ ማስገባት ይኖርበታል፣
6. ሎት 1 እና 2 የምትወዳደሩ ተጫራቾች የቫት ተመዝጋቢ መሆኑን አለባቸው፡፡
7. መ/ቤቱ የሚገዛውን እቃ ብዛት 20 % የመጨመርና የመቀነስ መብት አለው፡፡
8. መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብት አለው፡
9. ተጨማሪ መረጃዎችንና የጨረታ ሰነድ በአንፆ/ገ/ወ/ግ/ፋ/ን/አስ/ቁጥር 06 ማግኘት ይችላሉ፡፡

10 ውድድሩ የሚደረገው በእያንዳንዱ ሎት በጥቅል ድምር ዋጋ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር /0334440562/033 444 00 11 ይጠይቁ

ማሳሰቢያ :- የመክፈቻው ቀን በአል ላይ ከዋለ በሚቀጥለው በስራ ቀን ከላይ በተገለፀው ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡

**በአብክመ በሰ/ሸዋ/ዞን የአንፃ/ገ/ወ//ኢ/ ል/ት/ቤት ግፋ/በአስ/ ቡድን**



## ማስታወቂያ

እድገት የግራናይት አምራች ድርጅት በቤ/ጉ/ክ/መንግስት በአሶሳ ዞን ሆሞሻ ወረዳ ሸርቆሌ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የግራናይት ማዕድን ምርመራ ለማካሄድ በ2/01/2015 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡

**በመሆኑም በሚመለከተው ጅኦግራፊክ ኮርድኔት ክልል**

1.34° 35’ 08.376” E 10° 20’ 26.5884” N

2.34° 34’ 53.1912”E 10° 20’ 27.4740” N

3.34° 34’ 54.9624”E 10° 20’ 55.0104” N

4.34° 35’ 09.6756”E 10° 20’ 54.4992” N

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለኤጀንሲያችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡፡

**በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ**



## ማስታወቂያ

ቦንሾ ጠቅላላ ንግድ ስራዎች ኃ.የተ.የግ.ማህበር በቤ/ጉ/ክ/መንግስት በአሶሳ ዞን ሆሞሻ ወረዳ ሸርቆሌ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የግራናይት ማዕድን ምርመራ ለማካሄድ በ2/01/2015 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡

**በመሆኑም በሚመለከተው ጅኦግራፊክ ኮርድኔት ክልል**

1.34° 35’ 08.2860”E 10° 20’ 24.3024”N

2.34° 35’ 06.9720”E 10° 19’ 55.7436”N

3.34° 34’ 51.1896”E 10° 19’ 56.4852”N

4.34° 34’ 53.1372”E 10° 20’ 24.9756”N

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለኤጀንሲያችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡፡

**በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ**